አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3528 | ቅዳሜ ሐምሌ 5 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ፤ ገቢና ልማት

- የከተማዋ ገቢ እያደገ በመጣበት ልክ ልማቷም እየተፋጠነ መሆኑ ተገልጿል

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ2017 በጀት ዓመት ክንውን ሪፖርት ለከተማዋ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት

## የትውልድ ግንባታው ህያው ምስክሮች



8

ፎቶ- ከገፀ ድር

በ2017 በጀት ዓመት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል

## በደን ልማት ወሳኙ ምዕራፍ



4

ፎቶ- ከገፀ ድር

የብራዚል ደን ከፊል ገጽታ

## የጥበብ ጉልበት ለበጎ አድራጎት



13

ፎቶ- ከገፀ ድር

በአረንጓዴ አሻራ ዙሪያ ከተዘፈኑ ዘፈኖች መካከል የስንታየሁ በላይ ሙዚቃ አንዱ ነው

# “ቤት አዲስ” በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

- ሚዲያው የከተማዋ ብልሹ አሰራሮች የሚታረሙበትን መድረክ በማመቻቸት የልማቱ የጀርባ አጥንት እንደሆነ ተገለፀ



ፎቶ-ከፋይል

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ

በሳህሉ ብርሃኑ

መገናኛ ብዙሃን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ክንውኖችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለተደራሲያን የማድረስ ዋነኛ ዓላማ እና ኃላፊነት ይዘው ይመሰረታሉ፡፡ በየጊዜው ተደራሽነቱን እያሰፋ የመጣው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ለህብረተሰቡ ወቅታዊ፣ አስተማሪ፣ አዝናኝና አስጠንቃቂ መረጃዎችን የማድረስ ኃላፊነቱን በሚገባ እየተወጣ ይገኛል፡፡

ሚዲያው በመረጃዎቹና ፕሮግራሞቹ ተከታታዮቹን ከማስገንዘብ በተጨማሪ በቀጥታ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ይወጣል፤ በተለይ በማህበረሰብ ግንባታ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ለአብነትም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# “በምክክሩ ሂደት የማደርገውን ተሳትፎ አጠናክሬ እቀጥላለሁ”

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን

በስንታየሁ ምትኩ

በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ብሔራዊ መግባባት እንደሚያስፈልግ በተደጋጋሚ ጊዜ ሲነሳና ሲጠየቅ ቆይቷል፡፡ ብሔራዊ መግባባት ለማምጣት ያለሙ ውይይቶች በተለያዩ ዘጎችና ቡድኖች በጎ ፈቃድ ለማካሄድም ጥረት ተደርጓል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሂደቶች ውጤታማ ያልሆኑ ወይም ባክነው የቀሩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም የሂደቶቹ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል




# ርዕሰ አንቀፅ



## የከተማዋን ገቢ ማሳደግ ላይ መረባረብ ያስፈልጋል!

አዲስ አበባ የነበሩባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች እግር ከወርች አስረዋት የነዋሪውን ፍላጎት ማርካት፣ ያላትን ስም የሚመጥን ስራ መከወን ሳትችል ቆይታለች፡፡ ለዚህ የተጎሳቆሉ ገጽታዎቿን፣ ለማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የማይመቹ መንገዶቿን፣ መዳረሻ ሳይሆን መሸጋገሪያ እንድትሆን ያደረጓትን ተደብቀው የቆዩት የቱሪዝም ሀብቶቿን በማሳያነት መጥቀስ በቂ ነው፡፡

ከባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ከዚህ ድባቴ ወጥታ በተጨባጭ የሚታዩ፣ በሌሎች ሀገር ዜጎች ጭምር ምስክርነት የተቸራቸውን ስራዎች መስራት ችላለች፡፡ 3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤ ከትናንት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የአስተዳደሩን የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ሲያቀርቡ እንደገለጹት፣ ከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻ፣ የኮንቬንሽን እና ኤግዚቢሽን ማዕከል ለማድረግ በተሰራው ሥራ ከ150 በላይ ኮንፍረንሶች፣ ኤግዚቢሽኖችና ኤክስፖዎች ተካሂደዋል፡፡ በዚህም ከ1 ሚሊዮን በላይ  የውጪ ሀገር ቱሪስቶች ከተማዋን ጎብኝተው 143 ነጥብ 2 ቢሊዮን የሚሆን ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚዋ ፈሰስ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ከ9 ነጥብ 3 ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 55 ነጥብ 6 ቢሊዮን የሚሆን ገቢ ማግኘት ችላለች፡፡ ይህ ውጤት በኮሪደር ልማቱ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች፣ የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከልን ጨምሮ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ተጠናቅቀው አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው፣ የመዝናኛ አማራጮች መስፋታቸውና መሰል ስራዎች ያመጡት ውጤት ነው፡፡

ለከተማዋ ገጽታ መለወጥ፣ እየተገኘ ላለው ተስፋ ሰጪ ውጤት የገቢ አቅምን ማሳደግና በአግባቡ ማስተዳደር መቻል በመሰረታዊነት የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ ያልተሰበሰበው 8 ቢሊዮን ብር ከብድርና እርዳታ ይሰበሰባል ተብሎ በተጨማሪ በጀትነት የታወጀው ገና ገቢ ስላልተደረገ እንደሆነ የሚገልፀው የከተማ አስተዳደሩ ሪፖርት፣ የገቢ አሰባሰብ ንቅናቄ በመፍጠርና ጠንካራ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት በበጀት ዓመቱ ከ241 ቢሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ ታቅዶ 233 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 96 ነጥብ 5 በመቶ መፈፀም መቻሉን ያመላክታል፡፡  ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ደግሞ የ83 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ብልጫ ወይም የ57 በመቶ እድገት አሳይቷል። ይህ እየተሰበሰበ ያለው ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገት እያሳየ መምጣቱን ያመላክታል፡፡

እንደ ከተማ አስተዳደሩ መረጃ ከሆነ፣ በበጀት ዓመቱ ከ222 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ በወጪ ተመዝግቧል። የወጪ አፈጻጸሙ ለዘላቂ ልማት የሚመደበውን የመንግስት በጀት በ2016 ከነበረበት 57 ነጥብ 68 በመቶ በ2017 ወደ 71 ነጥብ 69 በመቶ እንዲያድግ አስችሎታል፡፡ ይህ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን አቅዶ ከመተግበር አንጻር ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለውን ውጤታማ እንቅስቃሴ በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡

የህዝብን ልማት ፍላጎት ለመመለስና የከተማዋን እድገት ለማረጋገጥ የገቢ አቅምን ማሳደግ አይተኬ ሚና አለው። ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀሰው በአዲስ አበባ ከተማ እንደመሆኑ መጠን ይህን እምቅ አቅም አሟጥጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በገቢ መሰብሰቡ ሂደት አማራጭ መንገዶችን ማማተር፣ ፈተና የሆኑትን ደግሞ ዘላቂ መፍትሄ በማበጀት መሻገር ያስፈልጋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ በ2018 በጀት ዓመት “የትኩረት አቅጣጫዎቼ ናቸው” ብሎ ከያዛቸው መካከል የገቢ አሰባሰቡን በማዘመን የገቢ እቅድ ማሳካት መሆኑ ደግሞ ለጉዳዩ የተሰጠውን ትኩረት በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡ ይህን ማድረግ የጋራ ርብርብን እንደሚጠይቅ ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት አያስፈልግም!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## የጋራ እንክብካቤ የሚሹት የጋራ ሀብቶቻችን

### ኤግል ከስድስት ኪሎ

በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎች ዘላቂ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ በተለይም በኮሪደር ልማት የለሙ የህዝብ መናፈሻዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የመንገድ ዳር መቀመጫዎች፣ የልጆች መጫወቻዎች፣ የህዝብ ፕላዛዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ፋውንቴኖች፣ የሳር ንጣፎች፣ ዕጽዋት፣ የመንገድ ዳር መብራቶች፣ የወንዝ ዳርቻዎች እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ከወጣባቸው ወጪና ተያያዥ ጉዳዮች አንጻር ዘላቂ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል  እላለሁ፡፡

በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ውበትን የሚጨምሩ እነዚህ የኮሪደር ልማት ውጤቶች መገንባታቸው ይበል የሚያሰኝ በጎ ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በከተማዋ ጎዳናዎች ላይ ስንቀሳቀስ በእነዚህ የልማት ስራዎች ላይ የተለያዩ ጉዳቶች ደርሰው አያለሁ። በመገናኛ ብዙሃን የተዘገቡ የከፉ ጉዳቶች መኖራቸውም ይታወቃል፡፡ በተለይ ለእግረኛ በተዘጋጁ መንገዶች በቸልተኝነትና በማን አለብኝነት ማሽከርከር፣ በብስክሌት መስመር ላይ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ በመንገድ ዳርቻ የተተከሉ የውበት እፅዋት እና የሳር ንጣፎችን መርገጥ እና ጉዳት ማድረስ ተደጋግሞ የሚስተዋል ድርጊት ሆኗል።

በተጨማሪም በለሙ ቦታዎች ላይ አፈር፣ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ብረት፣ ጠጠርና ሌሎች የግንባታ ግብዓቶችን ማከማቸት፣ በአውራ ጎዳናዎች ላይ ቆሻሻ ያለ አግባብ መጣል፣ የሞቱ እንስሳትና ደረቅ ቆሻሻዎችን ወደ ወንዞች መወርወር፣ የመንገድ ዳር መብራቶችን መጉዳትን የመሳሰሉ ጥፋቶችም ይስተዋላሉ፡፡

ከፍተኛ የገንዘብ፣ የጊዜ እና ጉልበት ወጪ ተደርጎባቸው በተሰሩ የልማት ውጤቶች ላይ የሚፈፀሙ እነዚህ ጥፋቶች ሊታረሙ ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ድርጊቱን በመከላከል ረገድ ደግሞ ሁሉም የየራሱን ኃላፊነት መወጣት አለበት፡፡ መንግስት ግንዛቤ በማስጨበጥ እና ጥፋተኞች ላይ አስተማሪ እርምጃ መውሰዱን ማጠናከር አለበት፡፡ ህብረተሰቡም በየአካባቢው ተገቢውን ጥበቃና ከለላ ማድረግ አለበት፡፡

በእርግጥ መንግስት እነዚህን የጥፋት ድርጊቶች በቀላሉ የሚያልፈው ጉዳይ አለመሆኑን እስከ አሁን ባሉት ጊዜያት በወሰዳቸው እርምጃዎች ከብደት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በኮሪደር የለሙ ቦታዎች ላይ ጉዳት በሚያስከትሉ አካላት ላይ የደንብ መተላለፍ ሲያጋጥም በየደረጃው የቅጣት ውሳኔዎችን አስቀምጦ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ስለመገኘቱ አመላካች ጅምሮች አሉ፡፡

በቅርቡ በካዛንቺስ የኮሪደር ልማት ላይ ጉዳት በማድረሱ የአንድ መቶ ሺህ ብር ቅጣት የተወሰነበት ግለሰብ ጉዳይ ማሳያ ነው፡፡ የህግ ጥሰት የፈፀመው ይህ ግለሰብ ሰፊ የመኪና መንገድ እያለ በእግረኛና በብስክሌት መንገድ ላይ በማሽከርከር በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ ለዚህ ጥፋቱም ተመጣጣኝ ቅጣት አግኝቷል፡፡ ከመንገድ ላይ የሰበሰቡትን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ወንዝ እየደፉ የተገኙ የጎዳና ላይ የፅዳት ሰራተኞች ላይም በተመሳሳይ አስተማሪ የገንዘብ ቅጣት መጣሉ ይታወሳል፡፡

ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ ተብለው በተሰሩ የልማት ስራዎች ላይ ጉዳት ማድረስ አግባብ አይደለም። ከፍተኛ በጀት ወጥቶባቸው የተሰሩ የኮሪደር መሰረተ ልማት ውጤቶችን መጠበቅ፣ መንከባከብና ከጉዳት ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ከነዋሪው የሚጠበቅ በመሆኑ ሁሉም የራሱን ኃላፊነት በመውሰድ እንደራሳቸው ንብረት መጠበቅ ይገባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ሄለን ጥላሁን
ሰገነት አስማማው

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ፤ ገቢና ልማት

- **የከተማዋ ገቢ እያደገ በመጣበት ልክ ልማቷም እየተፋጠነ መሆኑ ተገልጿል**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚሰበስበው ገቢ ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ ይገኛል፤ ከዓመት ዓመት በሰፊ ልዩነት ሲጨምርም ይስተዋላል፡፡ ለአብነት በ2013 ዓ.ም 42 ቢሊዮን ብር፣ በ2014 ዓ.ም ከተማዋ 55 ነጥብ 77 ቢሊዮን ብር፣ በ2015 ዓ.ም 108 ቢሊዮን ብር ሰብስባለች። በጀቷም በዚያው ልክ እየጨመረና ህዝባዊ ጠቀሜታ ያላቸው ግዙፍ የልማት ስራዎችን የመከወን ዕድል ተፈጥሯል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ2017 በጀት ዓመት ክንውን ሪፖርት ለከተማዋ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት

በ3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔ ላይ በአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የቀረበው ሪፖርትም እንደሚያሳየው በ2017 በጀት ዓመት 241 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ 233 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 96 ነጥብ 5 በመቶ ማሳካት ተችሏል። ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት 83 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው እንደማለት ነው፡፡

ወደ ኋላ መለስ ብለን የመዲናዋን የበጀት ዕድገት ለማሳያነት ብንመለከት በ2013 ዓ.ም 61 ቢሊዮን ብር የነበረ ሲሆን፣ ባለፉት ዓመታት በአራት እጥፍ ገደማ ለማደግ የፈጀበት አምስት ዓመት ብቻ መሆኑን እንመለከታለን። የ2018 በጀት ዓመትም ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ 350 ቢሊዮን ብር ቀርቦ ፀድቋል። በዋናነት ድህነት ቅነሳ ላይ ትኩረት ያደርጋል የተባለለት ይህ በጀት በተጨማሪም ለዘላቂ ልማት እና የሥራ ዕድል ለሚፈጥሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያነት እንደሚውል ተገልጿል። ለ2018 የተዘጋጀው በጀት ከ2017ቱ በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ108 ነጥብ 11 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው።

ከተማዋ በኢትዮጵያ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ ያላት፤ በራሷ ገቢ የምትተዳደር፤ ስማርት ሲቲ በመሆን ሂደት ውስጥ ያለች እንደመሆኗ ዓመታዊ ገቢዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ ያለው አንድምታ ምንድን ነው? በመዲናዋ እየተከናወኑ ካሉ የልማት ስራዎች አንጻር ምን ትርጉም አለው? በቀጣይ ዓመታትስ የከተማዋን የበጀት አቅም የበለጠ ለማሳደግ ምን መሰራት ይኖርበታል የሚሉና መሰል ጉዳዮችን መፈተሽ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚገልፁት ከሆነ ገቢ ለአንድ ሀገር ህልውና መሰረት ነው፡፡ በተለይ ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጭ የሚሰበሰብ ገቢ አስተማማኝ ልማትን የማረጋገጥ ዕድል ይሰጣል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሙያዊ ማብራሪያ የሰጡት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ዘካሪያስ ሚኖታ (ዶ/ር)፣ ልማትና ገቢ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ፡፡ ጠንካራ የበጀት ስርዓት ሲኖር ሰፋፊ የልማት ስራ ይኖራል፤ ልማቱ ሲያድግ ደግሞ በጀት የመሰብሰብ አቅምም እየጎለበት ይመጣል፡፡ የከተማዋም በጀት በየዓመቱ እያደገ የመምጣቱ አንደኛው ሚስጥር ይኸው ነው፡፡

**በ2017 ዓ.ም ከተማዋ 233 ቢሊዮን ብር ገቢ የሰበሰበች ሲሆን፣ ለ2018 ዓ.ም 350 ቢሊዮን ብር በጀት ይዛለች**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚያሳየው ከተማዋ ከታክስና ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የምትሰበስበው ገቢ ከዓመት ወደ ዓመት ከፍተኛ ጭማሪ እያሳየ መጥቷል፡፡ ለዚህም ለዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቶ መሰራቱ የራሱ ድርሻ እንዳለውና ፍሬያማ እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡ በሪፖርቱ መሠረት የቱሪዝም ዘርፉን ብቻ ነጥለን እንመልከት፡፡

መዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻ፣ የኮንቬንሽን እና ኤግዚቢሽን ማዕከል ከማድረግ ረገድ አበረታች ውጤት መመዝገቡ በሪፖርቱ ተገልጿል። በበጀት ዓመቱም በተካሄዱ ከ150 በላይ ኮንፍረንሶች፣ ኤግዚቢሽኖች እና ኤክስፖዎች ላይ ከተሳተፉ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በከተማ ደረጃ የተሻለ ገቢ ማግኘት መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አስረድተዋል።

ለዚህ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎች፣ የመንገድና የመሰረተ ልማት ስራዎች በየዓመቱ እያደገ ላለው የበጀት መጠን ድርሻቸው ወሳኝ ነው፡፡ የልማት ስራዎቹ መሰራታቸው ብቻም ሳይሆን በጥራት ተሰርተው በፍጥነት ወደ ስራ ስለሚገቡ ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸው የላቀ ነው የሚለውም የምጣኔ ሀብት መምህሩ አስተያየት ነው፡፡

እንደ መምህር ዘካሪያስ (ዶ/ር)፣ አስተያየት ከሆነ አሁንም ቢሆን ከተማዋ የሚገባትን የልማት ስራዎች እንድታገኝና በዓመቱ የገቢ ዕቅዷን ለማሳካት ከታክስና ከተለያዩ ምንጮች ገቢ ለማሳደግ የተለያዩ አማራጮችን መፈተሽ ያስፈልጋል። የመሰረተ-ልማት ግንባታ፣ ሰብዓዊ ልማትና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ከታክስና ከተለያዩ ምንጮች ገቢን መፈለግ የግድ ነው፡፡ አዲስ አበባ በርካታ አምራች ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋማትና ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚከናወንባት ከተማ በመሆኗ ሰፊ ገቢ የመሰብሰብ አቅም እንዳላትም መገመት አያዳግትም።

የተቀመጠውን የበጀት እቅድ ለማሳካት የገቢ አሰባሰብ ሰርዓትን የበለጠ ማዘመን እንደሚገባ አንስተዋል። ይህ ሲሆን ከተማዋ የጀመረቻቸውን ሜጋ ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ እንደ የቤት ልማት ፕሮግራሞችን፣ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት፣ የሌማት ትሩፋትና የከተማ ግብርናን ማስፋት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ያደርጋል በማለት መምህር ዘካሪያስ (ዶ/ር) አብራርተዋል፡፡

ሰኔ 26 ቀን 2017 ዓ.ም በተካሄደው የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 42ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ከተሞች 60 በመቶ ድርሻ እንዳላቸውና የአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ እንዳላት ተናግረው ነበር፡፡

ከ50 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለው በአዲስ አበባ ከተማ እንደሆነም አውስተው፣ አዲስ አበባ ላይ ካልተሠራ ይህን ኢኮኖሚ መጠቀም እንደማይቻል ገልጸዋል። “ከተማን ማነቃነቅ አጠቃላይ ሀብታችንን ማነቃነቅ ነው” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ እስከ አሁን አዲስ አበባ ላይ በተሠራው ሥራ ምንም ብድር እንዳልተወሰደም ጠቁመዋል። ይህም የከተማዋ ዓመታዊ በጀት በየጊዜው እያደገ ስለመምጣቱ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

እዚህ ጋር ታዲያ ለማሳያነት ይረዳ ዘንድ የተወሰኑ ዓመታትን የመዲናዋን የበጀት አሐዛዊ ቁጥሮችን እናክል፡፡ ከፍተኛ ጭማሪ እያሳየ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ በጀት፤ ከ2014 እስከ 2018 ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በ395 ነጥብ 25 በመቶ አድጓል። ይህም በ2014 ዓ.ም 70 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር የነበረው የከተማ አስተዳደሩ በጀት በአምስት ዓመት ውስጥ በአምስት እጥፍ ገደማ እንዳደገ ያመላክታል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በምክር ቤት ቀርበው ባቀረቡት ሪፖርት የተጀመሩ ተስፋ ሰጪና አበረታች ውጤቶችን በማስቀጠል በቀጣይ በትኩረት ይሰራባቸዋል ያሏቸውን ጉዳዮች አብራርተዋል፡፡

ከንቲባዋ በማብራሪያቸው የተጀመረውን ተቋማዊ ሪፎርም አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የገቢ አሰባሰብ ሰርዓትን የበለጠ በማዘመን፣ የገቢ እቅድን ማሳካት፣ እንዲሁም የቤት ልማት ፕሮግራሞችን በግል ዘርፉ፣ በሕብረት ሥራ ማኅበራት፣ በመንግስትና በግል የአጋርነት ፕሮግራም በስፋት ተግባራዊ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

አክለውም የውሃ አቅርቦትና ሌሎች የተጀመሩ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ እንደሚሰራና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት፣ የሌማት ትሩፋትና የከተማ ግብርናን ማስፋት፣ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል ብለዋል። የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራችን በተለይም የወጣቶች የሥራ አድል እና አምራች ኢንዱስትሪን የማስፋትና ተወዳዳሪነቱን የማሳደግ ስራ በልዩ ትኩረት ይከናወናል ሲሉም አክለዋል፡፡

# በደን ልማት ወሳኙ ምዕራፍ



ፎቶ- ከገፀ ድር
የብራዚል ደን ከፊል ገጽታ

**በደን ልማት ስራ ውስጥ የችግኝ ማፍላትና ጉድጓድ ቆፋሮን የመሳሰሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ሳይንሳዊ መሆን በጽድቀት መጠን ላይ በጎ ተጽዕኖ አላቸው**

በሳህሉ ብርሃኑ

ምድር በአስፈሪ ሁኔታ እየሞቀች ነው የሚለው መረጃ ከተሰማ ዓመታት ነጉደዋል፡፡ ምድር በአንድ ጎኗ በሙቀት ሳቢያ በሚመጣ የበረዶ መቅለጥ እና ጎርፍ ትጠቃለች፤ በሌላ ጎኗ ደግሞ በሰደድ እሳት እየተለበለበች ትገኛለች፡፡ ጎርፍ፣ ከባድ ሙቀትና አውሎንፋስ እያደረሱባት ያለው ጉዳት የዓለም መገናኛ ብዙሃንን የአየር ሰዓት ካጨናነቀም ሰነባብቷል፡፡

በአሜሪካ በደቡብ ምሥራቃዊ አቅጣጫ በምትገኘው ሉዚያና ግዛት አንስቶ በሩቅ ምሥራቋ ጃፓን ድረስ አውሎ ንፋስ እያደረሰ ያለው አደጋ ለዚህ አስረጅ ነው፡፡ ገፅታው ይለያይ እንጂ በአዳጊ ሀገራትም ላይ በርካታ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል።

በቅርብ ዓመታት ልዩነት እየተመላለሱ ምድርን የሚጎበኙ የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያታቸው ደግሞ በሰው ልጆች የሚተገበሩ የደን ጭፍጨፋዎች እና የበካይ ጋዝ ልቀቶች ስለመሆናቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ከመግለፅ ቦዝነው አያውቁም፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋነኛ መወያያ አጀንዳ ሆኖ በድርጅቱ ጠረጴዛ ላይ የተገኘውም ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ገደማ ነበር፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለመቋቋም ሀገራት ለስኬታማ የደን ልማት ስራ በቂ በጀትና ጊዜ መድበው እየሰሩ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ደቡብ ኮሪያ፣ ብራዚል እና ካናዳ በዓለም ላይ ትልቅ የደን ሽፋን ካላቸው ሀገራት በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናቸው። በዘላቂ የደን አስተዳደር ስራቸው በተደጋጋሚ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኙትን እንደ ስዊድን እና ፊንላንድ ያሉ የአውሮፓ ሀገራትን ሳንዘነጋ ማለት ነው። በተጨማሪም እንደ አውስትራሊያ እና ቻይና ያሉትም ከፍተኛ የደን መልሶ ማልማት ስኬት ያሳዩ ሀገራት ናቸው። ከአፍሪካም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ኢትዮጵያና ጋቦን ያሉ ሀገራት ዘላቂነት ያለው የደን አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የደን ልማት ስራን በጠንካራ ፖሊሲ ማገዝ፣ ወጥነት ያለውና ያልተቆራረጠ ስራ መስራት እና ለደን ልማት ስራ ወሳኝ ምዕራፍ ለሆነው የቅድመ ዝግጅት ስራ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በፔንስልቬንያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የደን ልማት ባለሙያ ቲያና ዱፖንት ያስረዳሉ። እርሳቸው እንደሚሉት ደግሞ የእነዚህ ሀገራት የስኬት ሚስጥር ይኸው ነው፡፡

ሀገራቱ የተሳካ የደን ልማት ስራ እንዴት ሊያከናውኑ ቻሉ? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ደቡብ ኮሪያን እንደምሳሌ ወስደው በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉት በጆርጂያ ዩኒቨርሲቲ የሰብል እና የአፈር ሳይንስ ክፍል ተመራማሪው ታይለር ዲንማን ተጨማሪ ማብራሪያ አላቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት ደቡብ ኮሪያውያን የደን ልማት ስራን የሚያከናውኑት በጠንካራ ፖሊሲና ሳይንሳዊ ምርምር ታግዘው ስለመሆኑ ያስረዳሉ፡፡

በእርግጥም ተመራማሪው ታይለር ዲንማን እንደፃፉት ከሆነ፣ ደቡብ ኮሪያ የኢኮኖሚ ልማትን ከአረንጓዴ ልማት ጋር በማጣጣምና ሀገራዊ አጀንዳ በማድረግ ፋር ቀዳጅ ሀገር ነች። እ.ኤ.አ በ2008 ኮሪያ 'ዝቅተኛ ካርቦን፣ አረንጓዴ እድገት' በሚል መርህ ከመካከለኛ እስከ የረጅም ጊዜ የልማት ራዕይ (ማለትም ከ2009 እስከ 2050) ይፋ አድርገው ነው ወደስራ የገቡት።

የደን ልማት ሂደቱ ከችግኝ ተከላ ጀምሮ ያሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ጠንካራ አሰራሮችን የዘረጋችው ደቡብ ኮሪያ የተሻለ ውጤት አግኝታበታለች፡፡ በተለይም ችግኞች በቂ ውሃ፣ ተገቢውን ብርሃን እና ሙቀት እንዲያገኙ በማድረግና ጥራት ያለው አፈር በማዘጋጀት ለተሻለ ውጤት መብቃታቸውን የአፈር ሳይንስ ተመራማሪው ታይለር ዲንማን ያብራራሉ፡፡

ችግኝ ማፍላትና ጉድጓድ ማዘጋጀት በፅድቀት ምጣኔ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን የሚጠቅሱት ተመራማሪው፣ ለኮሪያውያኑ የደን ልማት የስኬት ሚስጥርም እነዚህን ጉዳዮች ሳያዛንፉ መስራታቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የደን ስነ ምህዳር አስተዳደር ባለሙያ የሆኑት ቻይናዊው ሹ ዜንግ ታንግ በበኩላቸው፣ የችግኝ ተከላ ስራ ውጤታማ እንዲሆን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ወሳኝ ናቸው ይላሉ። ሊደረጉ የሚገባቸውን ዝግጅቶች ሲያብራሩም ችግኝ ከማዘጋጀት ጀምሮ ተከላና የእንክብካቤ ስራው ሳይንሳዊ እውቀትን መሰረት አድርጎ ካልተከናወነ የፅድቀት መጠኑ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በችግኝ ጣቢያዎች የሚፈሉ የዛፍ ዘሮችን በጥንቃቄ መምረጥ፤ የሚተከሉት ችግኞች ለምን ዓላማ የሚውሉ ናቸው? የእንጨት ውጤቶችን ለማምረት፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ የአፈርና ውሃ መሸርሸርን ለመከላከል ወይስ ለሌላ? የሚለውን ጉዳይ ማወቅና መለየት ይገባል ይላሉ፡፡

ባለሙያዎቹ እንደሚያስረዱትም ለተከላ የሚዘጋጀው ችግኝ በአግባቡ እንክብካቤ ተደርጎለት ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ቁመታቸው ከ40 እስከ 50 ሴንቲ ሜትር የደረሱ መሆን አለባቸው። ለተከላ ያልደረሱ ከሆኑ አቆይቶ በቀጣይ ዓመት እንዲተከሉ ማድረግ ይገባል። የጉድጓድ ቁፋሮው ቢቻል ከአንድ ወር በፊት ካልሆነም ከተከላው አሥራ አምስት ቀን ቀደም ብሎ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ ይህም የችግኝ መትከያ ጉድጓዱ በቂ እርጥበት እንዲይዝ ይረዳዋል፡፡ የችግኝ መትከያ ጉድጓድ ጥልቀቱም ከ30 እስከ 40 ሴንቲ ሜትር ቢሆን ይመረጣል፡፡ ጉድጓድ በሚቆፈርበት ጊዜ ከጉድጓዱ ተቆፍሮ የሚወጣውን የላይኛው አፈር ሳይበታተን ከጉድጓዱ ጎን መከመር ይኖርበታል፡፡

በችግኝ ጣቢያ የተዘጋጀ ችግኝ በሙሉ ለተከላ ብቁ ነው ማለት አይደለም የሚሉት ደግሞ በፔንስልቬንያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የደን ልማት ባለሙያ ቲያና ዱፖንት ናቸው፡፡ ባለሙያው ጉዳዩን ሲያብራሩም ለተከላ ያልደረሰ ችግኝ ቢተከል ከችግኝ ጣቢያ ውጭ ያለውን አካባቢና አረም መቋቋም ስለማይችል የጽድቀት መጠኑ አነስተኛ ይሆናል፡፡ ለተከላ የሚመረጥ ችግኝ የግንዱ ቁመት ከስሩ ቁመት በአማካይ ሁለት እጥፍ መብለጥና ጠንካራ ሊሆን ይገባል፡፡ ችግኙ በፈንገስ ወይንም በነፍሳት በአጠቃላይ በበሽታ ያልተጠቃና ጤናማ ሊሆን ይገባል፡፡ የተወላገደ ግንድ ያለው መጠኑ ከሚገባው በላይ ትንሽ ወይም ትልቅ የሆነ ችግኝ፣ ቅጠሉ ወደ ቢጫነት የተለወጠ ችግኝ ለተከላ ተገቢ አለመሆኑንና ቢተከልም የመጽደቅ ዕድሉ በጣም አነስተኛ እንደሚሆን አስፍረዋል፡፡

የደን ልማት ባለሙያው ቲያና አክለውም የችግኝ ተከላ ከመካሄዱ በፊት በቅድሚያ ጉድጓዱ ውስጥ የገቡ ባዕድ ነገሮችንና ውሃ ማውጣት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ችግኙ ጉድጓድ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ተለይቶ የተቀመጠውን የላይኛው አፈር እስከ ጉድጓድ ግማሽ (15 ሴንቲ ሜትር) ድረስ መመለስ ያስፈልጋል፣ ይህም የሚደረገው የመትከያው ጉድጓድ ከሚፈለገው በላይ ጥልቀት ያለው ከሆነ ችግኙ እንዳይቀበር ለማድረግና ጥልቀቱን ለማስተካከል ስለሚረዳ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ባለሙያዎቹ እንደሚገልፁት የደን ልማት ስራ ውጤታማ እንዲሆን ቢያንስ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ከግንዛቤ መግባት አለባቸው፡፡ እነዚህም ስራውን በጠንካራ ፖሊሲና ህግ ማገዝ፣ ወጥና ተከታታይነት ያለው ስራ መስራት እንዲሁም ሳይንሳዊ የሆነ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን መስራት የግድ ይላል፡፡ ይህ ካልሆነ ለበርካቶች ሕይወት መጥፋትና ንብረት መውደም ምክንያት የሆነው ወቅታዊው የዓለም ፈተና የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም የሚቻል አይመስልም፡፡

የጉዳዩን አሳሳቢነት ለመግለጽ ይረዳን ዘንድ አንዳንድ መረጃዎችን አቅርበን ጽሑፋችንን እንቋጭ፡፡ ዓለማችን በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበረችበት የሙቀት መጠን አሁን በ1 ነጥብ 2 ድግሪ ሴልሺዬስ ጨምራለች። ወደ አየር ንብረት የሚለቀቀው የካርቦን ዳይ አክሳይድ መጠን ደግሞ 50 በመቶ አድጓል። እንደ ዘርፉ ባለሙያዎች አስተያየት ከሆነ ደግሞ የምድራችን ሙቀት መጠን እንደ እ.ኤ.አ በ2100 ባለበት 1 ነጥብ 5 ድግሪ ሴልሺዬስ መቆየት አለበት። ነገር ግን አሁን ላይ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ካልተቻለ የምድራችን ሙቀት መጠን በያዝነው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ወደ 2 ድግሪ ሴልሺዬስ ከፍ ሊል ይችላል።

ባለሙያዎቹ አያይዘውም እንደሚገልጹት ችግሩን ለመግታት እርምጃ ካልተወሰደ እስከ 550 የሚደርሱ የእንስሳት ዝርያዎች በያዝነው ክፍለ ዘመን ሊጠፉ ይችላሉ። አስጊው ነገር ግን ይህ ብቻ አይደለም ይላሉ ሳይንቲስቶች። የሙቀት መጠኑ አሀዝ ወደ 4 ዲግሪ ሴልሺዬስ ከፍ ሊልም እንደሚችልና ይህ ማለት ደግሞ አስከፊ ሙቀት ተከስቶ ሚሊዮኖች በውሃ መጠን መጨመር ምክንያት ከመኖሪያቸው ሊፈናቀሉ እንደሚችሉ በተለይም እፅዋትና እንስሳት ከምድራችን ሊጠፉ እንደሚችሉም ጭምር እያሳሰቡ ይገኛሉ። ስለዚህ በደን ልማት ስራ ውስጥ ለችግኝ ፅድቀት መጠን ማደግ ወሳኝ በሆነው የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ላይ ማተኮር ተመካሪ ጉዳይ ነው።

ዜና ትንታኔ

## “ቤት ... ከገጽ 1 የዞረ

የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍ ረገድ ምሳሌ ሆኗል። የተቋሙን ሰራተኞች በማስተባበር በሚያገኘው ገቢ የበርካታ አዳጊዎችን የትምህርት ቤት ወጪ ይሸፍናል። በበዓላት ሰሞን በሚከናወኑ የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብሮች ላይ አስተዋፅኦ ያደርጋል፤ በተለያዩ ጊዜያት በተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ተገኝቶ እጅ ለአጠራቸው ወገኖች ደርሷል፤ በአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄም የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከመደበኛው የሚዲያ ስራዎቹና ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት ባሻገር ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባበር ዜጎችን የሚያስገነዝቡ፣ የሚያስተምሩና የሚያነቁ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተደራሽ ያደርጋል፡፡ በተለይ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ያጠነጠኑ ይዘቶችን ከተባባሪ አካላት ጋር በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የማድረስ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

ከሰሞኑም ከአዲስ አበባ ከተማ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን ስምምነት ተፈራርሟል፡፡ በሁለቱ ተቋማት የተደረገው ስምምነት “ቤት አዲስ” የተሰኘ ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በጋራ ለመስራት ነው፡፡ ፕሮግራሙ በየሳምንቱ የሚተላለፍ የ15 ደቂቃ ይዞታ ይኖረዋል፡፡

በውል ስምምነት መርሃ ግብሩ ወቅት መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ፣ የትውልድ ድምፅ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች መረጃዎችን ተደራሽ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸው፣ ተቋሙን ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ እየሰራቸው ያሉ ስራዎችን ለህብረተሰቡ በማድረስ እና ክፍተቶችን በመለየት ምላሽ እንዲያገኙ በትብብር እንደሚሰራ



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ እና የአዲስ አበባ ከተማ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ቅድስት ወልደጊዮርጊስ በጋራ የመስራት ስምምነትን በተፈራረሙበት ወቅት

የጠቆሙት አቶ ካሳሁን፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በቴክኖሎጂ፣ በአደረጃጀት እና በይዘት ሪፎርም እያደረገ እንደሚገኝም ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ቅድስት ወልደጊዮርጊስ በበኩላቸው፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የከተማዋ የጀርባ አጥንት እየሆነ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ቢሮው የተለያዩ የቤት ልማት አማራጮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እያደረገ እንደሚገኝ የገለፁት ወይዘሮ ቅድስት፣ እነዚህን ስራዎች ለማስተዋወቅ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ተመራጭ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡ በእስከ አሁኑ ሂደትም ቢሮው ለሰራቸው ስራዎች ሚዲያው ዐሻራውን ማሳረፉንም ጠቁመዋል።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የከተማዋ ብልሹ አሰራሮች የሚታረሙበትን መድረክ በማመቻቸት የልማቱ የጀርባ አጥንት እንደሆነ ተገልጿል።

ከዚህ ቀደምም አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት መፈራረማቸውም የሚታወስ ነው፡፡ ተቋማቱ በጋራ ለመስራት የተስማሙት “የሚሰሩ እጆች ወግ” የተሰኘ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሲሆን፣ የስራ ባህል ለማዳበር ብሎም በቂ የስራ ዕድል የሚፈጠርበትን መደላድል መፍጠርን ያለመ ስለመሆኑም በተፈራረሙበት ወቅት መገለፁ ይታወሳል፡፡

በእርግጥ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ ቀደምም ከተለየዩ ተቋማት ጋር በጋራ መስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ እሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጋር ተፈራርሞ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ከከተማዋ እድገት ጋር አብሮ ከፍ እያለ የመጣው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በህትመት እንዲሁም በዲጂታል አማራጮች መረጃዎችን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል። የትውልድ ድምፅ የሆነው ሚዲያው ተወዳደሪነት እና ተመራጭነቱን ለማሳደግ የጀመራቸውን የለውጥ ሥራዎች በማሳደግ የአድማጭ፣ ተመልካች እና አንባቢዎቹን ፍላጎት ለማርካትም እየተጋ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

በ2023 ተመራጭ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ የመሆን ራዕይን የሰነቀው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በአዲሱ የኤኤም. ኤን ፕላስ (AMN PLUS) የቴሌቪዥን ቻናሉ በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃዎችን ለህብረተሰቡ እያደረሰ እንደሚገኝ ተጠቁሟል፡፡

# ማስታወቂያ

### ጉዳዩ- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 12 በአቶ አዳሙ አንጀሎ ጃቤ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር B-278/09 ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር የካ/17657/08 የተሰጠበት ቀን 01/02/2008 ዓ/ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 26/10/2017 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ ታውጆ በ 30 ቀናት ውስጥ በይዞታው ላይ መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲያመጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው የተደረገ ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ምትክ ካርታ ተዘጋጅቶ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል።

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 04 አቶ ተሰማ ወልደፃዲቅ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር 670 ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000050401259 የተሰጠበት ቀን 27/12/2016 ዓ/ም እና የሴሪ ነበር R0157395 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቀን 14/05/2017 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን የይዞታ ካርታ መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 01488 በሴሪ ቁጥር 009973 በተኸሌ ታፈረ በርሄ ስም የተመዘገበው የይዞታና ቤት ባለይዞታነት እና ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

## 1ኛ ዙር ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

## ጨረታ ቁጥር 01/032/2018

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አስተዳደር ፋይናንስ ፅ/ቤት የሚከተሉትን እቃዎች ህጋዊ ድርጅቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች በዝርዝር በተገለፀዉ መስፈርት የሚያሟላ ማንኛዉም ነጋዴ መወዳደር ይችላል ፡፡

* የፅህፈት መሳሪያዎችና ሌሎች አላቂ እቃዎች
* አላቂ የፅዳት እቃዎች
* የደንብ ልብስ
* የቢሮ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች
* የህትመት
* አጠቃላይ የቢሮ ኤሌክትሮኒክስ ጥገና
* የፌርኒቸር ጥገና
* ሙሉ ዲኮር ስራ

ስለሆነም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መሳተፍ ይችላሉ

1. የዘመኑን ግብር መከፈላቸዉን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
2. በአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ በአቅራቢነት የተመዘገቡ መሆን እና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡
3. የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸዉ በተሰጣቸዉ የንግድ ዘርፍ ብቻ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ብቻ ዘወትር በስራ ሰአት የማይመለስ ብር 500 /አምስት መቶ ብር / በመክፈል ከወረዳዉ ፋይናንስ ፅ/ቤት ቢሮ ቁጥር 16 በመምጣት ሰነዱን ማግኘት ይችላሉ፡፡
6. ማንኛዉም ተጫራች ከታወቀ ባንክ የጨረታ ማስከበሪያ CPO በየሎቱ ስር በተቀመጠዉ ብር መሰረት ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ዋናዉንና ኮፒዉን በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማድረግ ጨረታዉ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት አየር ላይ የሚዉል ይሆናል፡፡ በአስራ አንደኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚያዉኑ ቀን 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ይከፈታል፡፡
8. ፅ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታዉን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡
9. ተጫራጮች የሚያቀርቡት የአንድ እቃ ዋጋ ቫትን ጨምሮ መቅረብ አለበት ፡፡
10. ተጫራቾች የሚጫረቱባቸዉን እቃዎች ናሙና የሚያስፈልጋቸዉ ከሆነ ጨረታዉ ከመከፈቱ በፊት ናሙና መግባት ይኖርበታል፡፡
11. ነጋዴዉ በጨረታ ሰነዶች ላይ ማህተም ሳያደርግ፣ ዋጋ ሳይሞላ፣ ስርዝ ድልዝ እና በፍሉድ የጠፋ ከሆነ እቃዉ ለዉድድር አይቀርብም፡፡
12. የጨረታ አሸናፊዉ ወይም ድርጅት ማሸነፉ እንደተረጋገጠ በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ቀርቦ ዉል መፈፀም አለበት ፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ 09 20 47 16 27 /09 13 07 04 12/ መደወል ይችላሉ።**

**አድራሻ ወረዳችን ቂ/ክ/ከ/ ወረዳ 01 ወደ ዉስጥ ገባ ብሎ ወደ ፒኮክ መናፈሻ መዉጫ መንገድ ይገኛል።**

---

በአቶ ረጋሳ በዳኔ ዋቄ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 011476/1 ሴሪ ቁጥር 024585 የቦታው ስፋት 279.62 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጅምሮ እስከ 20 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ት/ቤት**

---

ጊፍትያ ዘይኑ ሁሴን ስም በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ በቱሪስት ኮንዶሚኒየም ሳይት በካርታ ቁጥር ቦሌ/5/66/4/20/38443/00 በሴሪ ቁጥር 1473836 የተሰጠበት ቀን ----- የሆነ ማህደር በማህደር ክፍላችን ውስጥ ማግኘት ባለመቻሉ ማህደራቸውን ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት የይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ቀርበው እንዲያሳውቁ እየጠየቅን ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን በምትኩ ሌላ ማህደር የምናደራጅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ አልጋነሽ ገብረህይወት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100803805 የሴሪ ቁጥር 071677 በቀን 13/05/2013 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለው /ይዤዋለው/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትክ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሀሰን እንድሪስ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 281 ካርታ 04/66/13211/00 ተመዝግቦ የሚገኝ መዝገብ ቤት መገኘት የነበረበት ማህደር እና ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርእሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 713 አሰገደች ቀዮ ኮኖ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር አከ10/16/1/6954/አከ ሴሪ ቁጥር 007633 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 01/11/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውሰጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ በላይ አሰፋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ክልል ውስጥ የሚገኝ የይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 027948/2 የሴሪ ቁጥር 064629 የይዞታ ስፋት 1000 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/11/17 በቀን 01/11/17 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ከላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና እስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# “በምክክሩ ... ከገጽ 1 የዞረ

ከገጽ 1 የዞረ

አካታች አለመሆንና በስልጣን ያለው መንግስት ፈቃደኝነት ውስን መሆን እንደሚጠቀሱ በ1960ዎቹ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተሳተፉት፣ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሀሳባቸውን በማካፈል የሚታወቁት ደስታ መብራቱ (ፕሮፌሰር) “ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ መፍትሔ” በሚል ርዕስ ከፃፉት መፅሐፍ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን እውነታም ምሁራን፣ የሲቪክ ማህበራትና መንግስትን ጨምሮ ይጋሩታል፡፡

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ መንግስት ለሰው ህይወት መጥፋትና ለንብረት ውድመት ምክንያት የሆኑ ለዘመናት እየተንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት እንዲቻል ተነሳሽነቱን ወስዷል፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ለአለመግባባትና ልዩነት ምክንያት የሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮችን በመለየትና ምክክር በማድረግ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደሰፈረው፣ ሀገራዊ ምክክሩና የምክክሩ ሂደት በሚከናወንበት ወቅት ከግምት ውስጥ ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል አካታችነትና አሳታፊነት ይጠቀሳል፡፡

በግጭት አፈታትና የሰላም ግንባታ ጉዳዮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በአንድ ሀገር ላይ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ሁሉ ማሳተፍ ለውጤታማነት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ባለው ሀገራዊ ምክክር ሂደትም ህዝብን የሚወክሉ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ድምፃቸው እንዲሰማ፣ አጀንዳቸውን ለማካተት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል አካል ጉዳተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር ለማወቅ የሚያስችል በቅርብ የተሰራ ጥናት ማግኘት ባይቻልም፤ የዓለም ባንክና የዓለም ጤና ድርጅት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2011 በጋራ ያወጡት መረጃ እንደሚያሳየው፣ የአካል ጉዳተኞች ቁጥር ከጠቅላላው ህዝብ ውስጥ የ17 ነጥብ 6 በመቶ ወይም ወደ 20 ሚሊዮን ይገመታል፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች በባህል፣ በአመለካከትና ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘት አቅም እያላቸውና እየቻሉ፣ ምቹ ሁኔታዎች ባለመመቻቸቱ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በአግባቡ እንዲሳተፉ ባለመደረጉ ተጎጂ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ሀገርም በትክክል ማግኘት ያለባትን ጥቅም ሳታገኝ እንድትቆይ አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

የሰላም እጦት ሁሉንም ማህበረሰብ ይጎዳል፡፡ በተለይ ሰላም ባለመኖሩ በይበልጥ ለከፋ ችግር ተጋላጭ የሚሆኑት አካል ጉዳተኞ ናቸው ይላሉ በቅርቡ በፌዴራል ደረጃ በተካሄደው የባለድርሻ አካላት አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት የተሳተፉት፣ የኢትዮጵያ ዓይነ ስውራን ማህበር ፕሬዝዳንትና የቦርድ ሰብሳቢ አቶ አበራ ረታ፡፡

ሰላምን ለማስፈን የሚደረግ ማንኛውም ጥረት አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ ሀገራዊ ምክክሩም ዘላቂ ሰላምን በማምጣት አካል ጉዳተኞችን



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር አባላት የምክክር አጀንዳዎቹን ለኮሚሽኑ ሲያስረክቡ

ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ስራውን በሙሉ ልብ እንደሚደግፉት ይናገራሉ፡፡

በተለይ በፌዴራል ደረጃ የተካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ሰላም ሰላም በሚሸት፣ ዜጎች በሀገራቸው እምነትና ተስፋ እንዲኖራቸው ባደረገ መልኩ ነው፡፡ ከየትኛውም አካል የሚነሱ አጀንዳዎች ሳይጨፈለቁ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከቀረቡት አጀንዳዎች በይዘት የሚመሳሰሉትን ወደ አንድ በማምጣት የፌዴራል ባለድርሻዎች አጀንዳ ተብሎ እንዲያዝ ተደርጎል፡፡ ከአካል ጉዳተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች የቀረቡ አጀንዳዎች መያዛቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ሌላኛው ሀሳባቸውን ያጋሩን መቶ አለቃ በቀለ ጎንፋ ይባላሉ፡፡ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰራዊት አባል ናቸው። የሰላም እጦትና ግጭት ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል በተጨባጭ ከሚያውቁት መካከል ናቸው፡፡ ምክንያቱም በጦርነት ምክንያት ጓዶቻቸውን አጥተዋል፡፡ እርሳቸውም በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር በተደረገው ጦርነት አንድ እግራቸውን አጥተዋል፡፡ የሰላም እጦት፣ ግጭት፣ ጦርነት ዜጎችን ለአካል ጉዳትና ህልፈት እንዲሁም የንብረት ውድመት የሚዳርግ፣ የሀገርን እድገት ወደኋላ የሚጎትት በመሆኑ ለማንም የሚበጅ አይደለም ይላሉ፡፡

ግጭትና አለመረጋጋት ባለባቸው አካባቢዎች በተለይ አካል ጉዳተኞች ተጎጂ ናቸው፡፡ በነጻነት ሰርተውና ተንቀሳቅሰው መኖር፣ ከግጭት ማምለጥ አይችሉም፡፡ ጉዳቱ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብና ለወገንም ይተርፋል፡፡

ከዚህ አኳያ በሀገራችን ሰላምን ለማምጣት የሚደረጉ ጥረቶችን ሁሉ እንደሚደግፉ መቶ አለቃ በቀለ ያነሳሉ። ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የተያዘው ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም አካል ለሰላም እንቅፋት ናቸው የሚላቸውን መነሻ ምክንያቶች በመለየት ለኮሚሽኑ አጀንዳውን ማቅረብ ይገባዋል። በምክክሩም ለልዩነትና ግጭት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በደንብ ለይቶ በማውጣት፣ በሰከነ መንገድ በመወያየት መግባባት ላይ መድረስ እንደሚቻል መቶ አለቃ በቀለ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን የኮሙኒኬሽን ክፍል ኃላፊ አቶ ታደሰ መሸሻ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ማረጋገጥ አካል ጉዳተኞች አጥብቀው የሚሹት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም አካል ጉዳተኞች ባለባቸው የአካል ጉዳት ሮጦ ማምለጥ፣ መረጃ አግኝቶ ራስን መጠበቅና መከላከል ስለሚያዳግታቸው ተጎጂዎች ናቸው፡፡

ሌላው የአካል ጉዳተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች የአካታችነት ጥያቄ በአግባቡ ባልተመለሰበትና የተለያዩ ችግሮች እየተጋፈጡ በሚኖሩበት ሁኔታ ግጭት መኖር ተጨማሪ አካል ጉዳተኛ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሀገራዊ ምክክሩ ዘላቂ ሰላምና የተረጋጋ ሀገር ለመፍጠር ሁነኛ መንገድ መሆኑን በመረዳት በሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሆነ አቶ ታደሰ ያነሳሉ፡፡

አጀንዳ በማሰበሰብ ሂደት በክልልም ሆነ በፌዴራል አካል ጉዳተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ማህበራት ፌዴሬሽን ስር ከሚገኙ ማህበራት፣ ባለሙያዎች፣ የአካል ጉዳተኛ መብት ተሟጋች ግለሰቦች ጋር በመመካከርና በማሳተፍ ሶስት ጥቅል አጀንዳዎች ተለይተው በአጀንዳ እንዲያዙ መደረጋቸውን አቶ ታደሰ አስረድተዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ ሀገራዊ እንዲሁም ከራሳቸው ከአካል ጉዳተኞች ጋር በተያያዘ በመላ ሀገሪቱ የጋራ አቋም በመያዝ፣ ሁለተናዊ ተሳትፏቸውን የሚያሳድጉ፣ አካታችነትን የሚያረጋግጡ አጀንዳዎችን አቅርበዋል። በሀገራዊ ምክክሩ ከቀረቡና ከተያዙ አጀንዳዎች አንዱ በሀገሪቱ የአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎ ወይም ውክልና የማረጋገጥ ጉዳይ ይገኝበታል፡፡ በክልልና በፌዴራል በሶስቱም የመንግስት አካላት በህግ አውጪው፣ ህግ አስፈፃሚና ተርጓሚ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ጨምሮ በተለያዩ እርከኖች የአካል ጉዳተኛውን ማህበረሰብ የሚወክል መቀመጫ እንዲኖር የሚጠይቅ አጀንዳ ነው፡፡ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንደሚገልፁት አካል ጉዳተኞች ውክልናቸው ሲረጋገጥ በራሳቸው ጉዳይ የመወሰን፣ የሚፈጠሩ የፖሊሲ ወይም የህግ ክፍተቶችን የማስተካከል ዕድል ያገኛሉ፡፡

ሌላው የአካል ጉዳተኞችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ከህገ መንግስቱ ጀምሮ የወጡ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች አካል ጉዳተኞችን በተገቢው ሁኔታ ያካተቱ እንዲሆኑ ማሻሻያ እንዲደረግ የተጠየቀበት ጉዳይ ይገኝበታል፡፡ ይህንን አቶ ታደሰ ማሳያ ይሆናል ያሉትን ነጥብ በማንሳት ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ “መንግስት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል” በሚል ተቀምጧል፡፡ እዚህ ላይ መንግስት “አቅም በፈቀደ መጠን እንክብካቤ ያደርጋል” የሚለው ለትርጉም ክፍት የሆነ፣ አንዳንድ አካላት የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ለማካተት “አቅም የለኝም” በሚል ጥረት ባያደርጉ ተጠያቂ የማያደርግና አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ ሊሻሻል ይገባዋል ይላሉ፤ አቶ ታደሰ፡፡

በምክክሩ በአጀንዳ እንዲያዝ የቀረበውና ተቀባይነት ያገኘው ሶስተኛው ጉዳይ በአካል ጉዳተኞች ባለቤትነት የሚመራ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲመሰረት የሚጠይቅ ነው፡፡ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ነው የሚመራው፡፡ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራበት በኤጀንሲ ወይም በሆነ ተቋም ደረጃ የተደራጀ፣ ነፃና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ለማስፈፀም፣ የወጡ ፖሊሲዎችንና ህጎችን የሚፈፅም፣ የሚቆጣጠርና የሚከታተል ተቋም እንዲኖር ተፈልጎ እንደሆነ አቶ ታደሰ አስረድተዋል፡፡

በምክክሩ ሂደት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር ጋር በተያያዘ አቶ ታደሰ እንደሚያነሱት መጀመሪያ አካባቢ አንዳንድ የውይይት ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አልነበሩም፡፡ የምልክት ቋንቋ በበቂ ሁኔታ አለመመደብ ችግር ነበር፡፡ ችግሩን ቀድሞ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በማሳወቅና በቅርበት በመነጋገር በሂደት መፍትሔ እየተሰጠው መጥቷል። “በምክክር ሂደቱ አካል ጉዳተኞችን በማካተትና ተደራሽ በማድረግ ያን ያህል የሚባል የጎላ ችግር አልገጠመንም፡፡ በበቂ ሁኔታ ተሳትፎ አድርገናል” ብለዋል፡፡

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ባካሄዳቸው የአጀንዳ ማሰባሰቢያ መድረኮች በእያንዳንዱ በክልል ደረጃ እስከ 26 የሚደርሱ አካል ጉዳተኞች አጀንዳ በማሰባሰብ ሂደት ተሳትፈዋል፡፡ በፌዴራል ደረጃ በተካሄደው የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ 21 የሚደርሱ አካል ጉዳተኞች መሳተፋቸውን አቶ ታደሰ ጠቁመዋል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የትውልድ ግንባታው ህያው ምስክሮች

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት ዳግማዊ ተሰማ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ነዋሪ ነው፡፡ ደረጃውን ጠብቆ ተገንብቶ ሰሞኑን ለአገልግሎት ክፍት በሆነው የዳግማዊ ምኒልክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ኳስ ሲጫወት ነው ያገኘነው፡፡ ከዚህ ቀደም በትርፍ ጊዜው ኳስ ይጫወት የነበረው ጃንሜዳ እየሄደ እንደነበር ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ "ሜዳው የተስተካከለ ባለመሆኑ ስወድቅ ጉዳት ያጋጥመኝ ነበር፡፡ ክረምት ሲመጣ ደግሞ ውሃ ስለሚያቁርና ጭቃ ስለሚሆን አንጫወትም" ሲል አስተያየቱን አጋርቷል፡፡

የሽሮ ሜዳ ነዋሪው ወጣት አቤል ብዙአየሁ በበኩሉ እንደገለጸው፣ ከዚህ ቀደም በአካባቢያቸው ኳስ እና የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉባቸው ሜዳዎች ቢኖሩም ምቹ አልነበሩም፡፡ ደረጃቸውን ያልጠበቁ፣ የተስተካከለ የሳር ንጣፍ የሌላቸውና አቧራማ በመሆናቸው ለጉዳት የሚያጋልጡ ነበሩ፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆን የመንገድ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቤትና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ካለው ፍላጎትና ከተማዋ ማቅረብ ከሚጠበቅባት አኳያ ሲታይ ብዙ ክፍተቶች ነበሩ፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ይህን ጥያቄ እና ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደረጉ፣ የከተማዋን ገጽታም የቀየሩ ስራዎች ተሰርተዋል፤ በመሰራት ላይም ናቸው፡፡

## ለአገልግሎት እየበቁ ያሉ ፕሮጀክቶችና ፋይዳቸው

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤና በከተማዋ ከፍተኛ ኃላፊዎች ተመርቀው ለህዝብ ክፍት እየሆኑ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል 122 የወጣቶች ስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችና 1 ሺህ 155 የቀዳማይ ልጅነት ልማት (የህፃናት መጫወቻ ቦታዎች) ይጠቀሳሉ፡፡

ወጣቶቹ ዳግማዊና አቤል ደረጃውን የጠበቀ እግር ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ ሩጫና የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ የሚያስችሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በመገንባታቸው በጣም ደስተኛ እንደሆኑ ነግረውናል። የእግር ኳስ ሜዳው በተመቸ ሁኔታ ኳስ መጫወት እንድንችል፣ ያለንን ትርፍ ጊዜ ከአልባሌ ቦታዎች ርቀን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እንድናሳልፍ ያግዘናል፡፡ ሌሎች አዳጊዎች ከአልባሌ ቦታ ርቀው ትርፍ ጊዜያቸውን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ጤንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ረገድ አይተኬ ሚና እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

ከሰሞኑ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ተገንብተው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን የመረቁት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ ዛሬ ያልዘራነውን ነገ ልናጭድ ስለማንችል የከተማ አስተዳደሩ ልጆች ከህፃንነታቸው ጀምሮ ተገቢውን እውቀት፣ ፍቅርና ክብር አግኝተው እንዲያድጉ በጀት በመመደብ ለህፃናት ማቆያዎችና የስፖርት ማዘውተሪያዎች ትኩረት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶሺዮሎጂና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ክቡር እንግዳወርቅ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፣ የተገነቡ ህጻናትንና ወጣቶችን ታሳቢ ያደረጉ ፕሮጀክቶች እንደማህበረሰብ ጥናት ተመራማሪ ሲናፍቋቸው የነበሩና በጥናት አስደግፈው እንዲሰሩ ምክረ ሀሳብ ሲያቀርቡባቸው የነበሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

አዲስ አበባ ሰዎች ተጠጋግተው የሚኖሩባት፣ ብዙ መዝናኛና መተንፈሻዎች የሌላት፣ የተሻለ አቅም ያላቸው ወላጆች ካልሆኑ በስተቀር ብዙዎቹ ልጆቻቸው የሚውሉባቸውና የሚዝናኑባቸው ስፍራዎች ያልነበሯት ከተማ ነበረች፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ የህፃናት ማቆያዎችና የስፖርት ማዘውተሪያዎች መስፋፋታቸው በአካል፣ በአዕምሮና ስነ ልቦና ጤናማ የሆነ ትውልድ ይፈጥራል፡፡

ወጣቶችን ብንወስድ በቁጥር ግዙፍ፣ ባለ ብሩህ አዕምሮ፣ አምራች ሀይል፣ የነገ ሀገር ገንቢና ተረካቢ ናቸው፡፡ ካሉበት የዕድሜ ክልል አኳያም ለተለያዩ ውስብስብ ችግሮች ተጋላጭ ናቸው፡፡ ሱስ ውስጥ መዘፈቅ፣ በተለያየ ምክንያት ተስፋ መቁረጥ፣ ራስን መጉዳት ወይም ማጥፋት ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች የሚያሳልፉ ከሆነ ግን ስፖርት እየሰራ፣ እያነበበና እየተዝናና በአካልና በአዕምሮ የጎለበተ፣ መፍጠር የሚችል፣ የተሻለ ነገን የሚናፍቅና የሚያልም ትውልድ ይሆናሉ ይላሉ፤ ክቡር (ዶ/ር)፡፡

ህፃናትና ወጣቶች በተሰሩላቸው የመዝናኛና ማሳለፊያ ጊዜዎች ሲጠቀሙ "የእኔ ሀገር ናት የሰጠችኝ፤ የእኔ ቦታዎች ናቸው" በሚል ባለቤትነታቸው ያድጋል፡፡ ለስፍራዎች ያላቸው ፍቅርና የእኔነት ስሜት ይዳብራል፡፡ በራሳቸው ተነሳሽነትም ይጠብቃሉ፡፡ አልፎ ተርፎም ከተማቸውንና ሀገራቸውን ይወድዳሉ ብለዋል፡፡ ልማቶቹ እንደ ከተማ ማህበራዊ እኩልነትን ለማስፈን የሚያስችሉ መሆናቸውንም አክለዋል፡፡

የስነ ልቦና ባለሙያዋ ወይዘሮ ትዕግስት ዋልተንጉስ ከደራሲ ቴዎድሮስ ተክለአረጋይ ጋር ባሰናዱት "ምን ሆኛለሁ" በተሰኘው መጽሐፍ ላይ እንዳሰፈሩት፣ የወጣቶች መጫወቻና መዝናኛ ቦታዎች በነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ግንባታ ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ አንድ ሰፈር ውስጥ ያለ የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ፈርሶ ፎቅ ሲሰራበት፣ ፎቁ ጥቅም የሚሰጥ ቢሆንም፤ ለልጆቹ ተለዋጭ ቦታ ካልተዘጋጀ የእነሱን አንድ ማህበራዊ ተቋም ማፍረስ ነው የሚሆነው፡፡ እንዲህ ዓይነት አካሄድም ቶሎ የሚከፋው፣ ቶሎ የሚደብረው፣ ቶሎ ተስፋ የሚቆረጥ ልጅ እንዲበራከት ያደርጋል፡፡ ልጆች በጨዋታ የሚገናኙበትና የሚጎዳኙበት ሁኔታ መፍጠር ትልቅ የማህበራዊ ተቋም ግንባታ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር
በ2017 በጀት ዓመት ተጠናቅቀው አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ፕሮጀክቶች በከፊል

በከተማዋ ለአገልግሎት ክፍት እየሆኑ ያሉት ፕሮጀክቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ የአዲስ አበባ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን በትናትናው ዕለት ማካሄድ በጀመረበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩን የ2017 በጀት ዓመት ሪፖርት አፈፃፀም ያቀረቡት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ በከተማዋ በ2017 በጀት ዓመት 15 ሺህ 960 ጉልህ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ ፕሮጀክቶች፣ የመኪና ማቆሚያዎች፣ መስሪያ ሼዶች፣ ቤቶች ይገኙበታል፡፡

በሁለተኛ ምዕራፍ የኮሪደር ልማቱም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው አገልግሎት የሚሰጡ ልማቶች እየተመረቁ ይገኛሉ። ለአብነትም ሰፊና ምቹ የሆነ የእግረኛ መንገድ በመገንባቱ ሰዎች በእግራቸው እና በሳይክል ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ የሚሉት ክቡር (ዶ/ር)፣ ይህም ጤናማ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያግዛል፡፡ ሰዎች ጥሩ ነገሮችን ሲመለከቱ አስተሳሰባቸው አዎንታዊ የመሆን፣ ለከተማና ለሀገር ያላቸው ፍቅር በመጨመር አዎንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከሁለት ወር በፊት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የተናገሩት ሀሳብ ይህንን የሚያጠናክር ነው፡፡ "ከ80 በመቶ እጅ በላይ በእግር የሚሄድ ሰው ባለበት ከተማ ውስጥ መንገድን ለተሽከርካሪ ብቻ ልናደርግ አንችልም፡፡ እግረኛው በእግር መሄድን ባህል እንዲያደርግና ማህበራዊ መስተጋብር እንዲዳብር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡" ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሶሲዮሎጂና አንትሮፖሎጂ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን ዱዳ (ዶ/ር) እንዲሁ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችም ንቁ የትራንስፖርት ዘዴዎችን ማበረታታት ብቻ ሳይሆን ሕያው የመንገድ ላይ እንቅስቃሴን በመፍጠር ድንገተኛ ግንኙነቶችን ይጨምራሉ፡፡ እንዲሁም ከተማዋ የበለጠ የተገናኘች እና ሰብአዊ የሆነ መልክ እንዲኖራት ያደርጋሉ። በጥቅሉ ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር ይፈጥራሉ፤ የጋራ መግባባትን ያሳድጋሉ፣ እንዲሁም የማህበረሰብ ችግሮችን የመቋቋም አቅምን በመገንባት ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖራቸው ያስረዳሉ፡፡

ህዝብ በጋራ የሚጠቀምባቸው መሰረተ ልማቶች አካላዊ ጤናን በማበረታታት የህዝብ ጤና ላይ በቀጥታ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው ዘሪሁን (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡ በተለይ ለህፃናትና ወጣቶች አካላዊ እድገት፣ ለማህበራዊ ክህሎትና የፈጠራ አስተሳሰብ መጎልበት አስፈላጊ ናቸው፡፡ ለመዝናኛ፣ ለመማር አሳታፊ ቦታዎችን ማቅረብ ወጣቶች ከአልባሌ ቦታ ርቀው ጊዜያቸውን በአዎንታዊና በሚጠቅም መልኩ እንዲያሳልፉና ጉልበታቸውን ገንቢ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ የህዝብ የጋራ መገልገያዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ቀጣዩን ትውልድ የሚቀርፀው ጤና፣ ትምህርትና ማህበራዊ መስተጋብር ላይ መስራት ማለት ነው፡፡

ህዝብ በጋራ የሚጠቀምባቸውና የሚገናኝባቸው ስፍራዎች ከተለያየ የአስተዳደግ ባህል የመጡ ሰዎች መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ የሚያገናኙ ተፈጥሯዊ መሰባሰቢያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ አረንጓዴ ስፍራዎችና መዝናኛዎች ለመዝናናት፣ ለመንቀሳቀስ እንዲሁም ለመገናኘት ዕድል በመፍጠር በከተማ አካባቢዎች ውስጥ ሊደበዝዝ የሚችለውን የማህበረሰብ ትስስር በመቀነስ የመቀራረብ ስሜት ያዳብራሉ፡፡

አንድ ከተማ ወደ ንፁህ፣ ሙሉ መሰረታዊ መሠረተ ልማት ወዳለው፣ ዘመናዊና ለኑሮ ምቹ ወደሆነ አካባቢ መለወጡ ጤናማ ማህበረሰብን ከመፍጠር በተጨማሪ የተሻሉ እድሎችን ማቅረብ ያስችላታል፡፡ የተሻሻለ መሠረተ ልማት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ይደግፋል፤ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ውብና ምቹ የከተማ ቦታዎች አጠቃላይ የኑሮ ጥራትን ያሻሽላሉ፡፡ ይህም የነዋሪዎችን ደስታና ደህንነት ያሳድጋል። ትውልዱ በእንደዚህ ዓይነት አካባቢ ማደግ የላቀ የዕድል ደረጃን ይፈጥራል፣ ለእድገታቸው የተሻለ የሀብት ተደራሽነትን ይሰጣል እንዲሁም በከተማቸው ላይ የኩራትና የባለቤትነት ስሜትን ያሰርፃል። የበለጠ የበለፀገ እና ዘላቂነት ያለው የወደፊት ዕጣ ፈንታን በመቅረፅ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለውም ዘሪሁን (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

በጥቅሉ በከተማዋ ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት እየሆኑ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የነዋሪዎችን የረጅም ጊዜ ጥያቄዎች የሚፈቱ ናቸው፡፡ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ አካል የሆኑ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እና አጠቃላይ የከተማዋን ነዋሪዎች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የሚሰራው ስራ ምስክር ናቸው ብሎም መውሰድ ይቻላል፡፡

# አገልግሎቱ ለተገልጋዩ ምን ያህል የቀረበ ነው?

- ከ482 ሺህ በላይ የንግዱ ማህበረሰብ ማህደር በዲጂታል መንገድ ተደራጅቷል

**በሰገነት አስማማው**

አዲስ አበባ በሁለንተናዊ መስክ ከዘመኑ ጋር የምትራመድ ከተማ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ፤ በተለያዩ መስኮችም አስደናቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው። አሁንም ሰፊ ስራ ከሚጠይቁና ህዝብ ጥያቄ ከሚያነሳባቸው ጉዳዮች መካከል የአገልግሎት አሰጣጡ ይጠቀሳል፡፡

በመዲናዋ የመንግስት አገልግሎትን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ግልፅነትን የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለመስጠት የሚደረገው ጥረት ይጠቀሳል።

የአዲስ አበባ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን በትናንትናው ዕለት ማካሄድ በጀመረበት ቀን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት በከተማዋ 347 አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡

በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው የከተማዋ ተቋማት መካከል የንግድ ቢሮ አንዱ ነው። ለመሆኑ የንግዱ ፈቃድ፣ እድሳትና ተያያዥ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ በመስጠት ረገድ ምን እየተሰራ ነው? ምን ውጤት እየተገኘ ነው? ስንል ተገልጋዮችንና የንግድ ዘርፍ ኃላፊዎችን በማነጋገር እንደሚከተለው ዳሰስነዋል፡፡

“ቀድሞ የነበረው የንግድ ፈቃድና እድሳት አገልግሎቱ አሰልቺ፣ ምልልስም የሚበዛበት ነበር፡፡ አሁን አሰራሩ በቴክኖሎጂ መደገፉ አገልግሎቶችን ከሰው ንክኪ በፀዳ ሁኔታ በእጅ ስልካችን በሲስተም እንድናገኝ አስችሎናል፡፡ ንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (ቲን) በስልኬ በሲስተም ነው ያወጣሁት። አገልግሎቱ ዘምኗል” ሲሉ የገለፁት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት የንግድ ፍቃድ ለማደስ በመጡበት ወቅት ያነጋገርናቸው አቶ አባይ ካሳ ናቸው፡፡

ወይዘሪት አይዳ ዘካሪያስም በጽህፈት ቤቱ ንግድ ፈቃድ ለመመለስ መምጣቷንና ባለሙያዎች ጥሩ መስተንግዶ እንዳደረጉላት ገልጻለች፡፡ “ከአምስት ዓመት በፊት አገልግሎት ለማግኘት በተደጋጋሚ እመላለስ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በኦንላይን ማግኘት መቻላችን ምልልስን በማስቀረት ጊዜና ጉልበትን ቆጥቦልናል” ስትል ያለውን ለውጥ በንጽጽር አብራርታለች፡፡

ወይዘሮ ጽዮን ዮሴፍ ለተለያዩ አገልግሎቶች ወደ አራዳ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት እንደሚመጡ ነግረውናል፡፡ “የንግድ ፈቃዴን ወደ ሌላ ክፍለ ከተማ ለማዘዋወር ነበር የመጣሁት፡፡ ምንም የገጠመኝ ችግር የለም፡፡ በጥሩ መስተንግዶና በፈጣን ሁኔታ ነው አገልግሎቱን ያገኘሁት፡፡” ሲሉም ገልፀዋል፡፡

አቶ ሲሳይ ጎሳዬም፤ “ቀድሞ በነበረው አገልግሎት አሰጣጥ ባለሙያው



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በአራዳ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት አገልግሎት ሲሰጥ

አገልግሎት ፈልገን የምንመጣ አይመስለውም ነበር፡፡ አሁን እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ከበፊቱ ጋር ፈፅሞ አይገናኝም፡፡ በአክብሮት ነው የሚያገለግሉን፡፡ ንግድ ፍቃድ በኦንላይን ለማውጣት ሂደት ጀምሬአለሁ፡፡ ለተጨማሪ አገልግሎት ነው የመጣሁት። ከጊዜም፣ ከገንዘብም አንፃር አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ታግዞ መሰጠቱ ያጋጥም የነበረውን እንግልት አቅልሎልናል” ሲሉ በአገልግሎቱ መርካታቸውን ይናገራሉ፡፡

የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በሁለቱ ክፍለ ከተሞች ንግድ ጽህፈት ቤቶች በቴክኖሎጂ ተደግፎ ለህብረተሰቡ እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት አስመልክቶ ኃላፊዎችን አነጋግሯል፡፡

የጉለሌ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አንዱአለም ክብረት በሰጡት መረጃ፣ የንግድ ፈቃድ ማውጣት፣ የንግድ ፈቃድ መሰረዝ፣ ስም ማፀደቅና ሌሎችም አገልግሎቶች ህብረተሰቡ ወደ ጽህፈት ቤቱ መምጣት ሳይጠበቅበት በኦንላይን ነው የሚሰጡት፡፡ ከዚህ ባለፈ የገበያ ዋጋ መረጃ በመሰብሰብ የኦንላይን የገበያ መረጃ የመስጠት፣ “ማኬባ” በሚባል ህጋዊ ፈቃድ ባለው የንግድ ድርጅት አማካኝነት መሰረታዊ የሸቀጥ ስርጭት አገልግሎት በቴክኖሎጂ ታግዞ ይሰጣል። ህብረተሰቡ በሲስተም እንዲመዘገብ ተደርጎ ድርጅቱ በአድራሻው ቤት ለቤት መሰረታዊ ሸቀጦችን ያቀርባል፡፡ በዚህም ወደ 40 ሺህ በላይ የሚሆኑ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ በወረቀት የነበሩ 42 ሺህ የንግዱ ማህበረሰብ ማህደር ስካን በማድረግ በዲጂታል መንገድ ተደራጅቶ ኦንላይን ገብቷል፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ የተተገበረ ነው፡፡ መረጃዎች በሶፍት ኮፒ መያዛቸው ማህደሮች እንዳይጠፉና እንዳይበላሹ ያስችላልም ብለዋል፡፡

አብዛኛው አገልግሎት የሚሰጠው በቴክኖሎጂ እንደመሆኑ መጠን የኔትዎርክ መቆራረጥ ቢያጋጥም ድጋፍ የሚያደርግ ክፍል ተደራጅቶ ይገኛል። በቴክኖሎጂ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማያውቅ የህብረተሰብ ክፍል ስለሚኖር ግንዛቤ የመስጠት፣ ቴክኖሎጂው አዲስ የሆነበት ተገልጋይ ሲመጣ እገዛ የማድረግ እንዲሁም በበራሪ ወረቀት መረጃን የማሳወቅ ስራም እንደሚሰራ አቶ አንዱአለም ገልፀዋል፡፡

ሁሉም አገልግሎት በቴክኖሎጂ መሰጠቱ ብልሹ አሰራር እንዲቀንስ ያደርጋል የሚሉት ኃላፊው፣ በ2017 በጀት ዓመት 3 ባለሙያዎች ያለ ፈቃድ በመቅረት ምክንያት ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ የቃልና የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል” ሲሉ ከቴክኖሎጂው ባሻገር ስለሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ስለተወሰደው የእርምት እርምጃ ጠቁመዋል፡፡

የንግዱ ማህበረሰብ አገልግሎትን በተገቢው እንዲያገኝ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ ሲሆን ህብረተሰቡም በንግድ ስርዓቱ የሚያጋጥም ህገ ወጥነትን ከመከላከል አኳያ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት እንዳለበት ኃላፊው መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ በላይነህ ሙሉጌታ በተመሳሳይ በሰጡት መረጃ፤ የቅድመ ሂሳብ መተንተን ማፅደቅ፣ የድርጅት ስም ማጣራት፣ የድርጅት ስም ማሻሻልና ሌሎችም በኦንላይን ይሰጣሉ፡፡ ህብረተሰቡ ወደ ጽህፈት ቤቱ ሳይመጣ በእጅ ስልኩ ብቻ የንግድ ፈቃድ እና እድሳት በኦንላይን አገልግሎቱን ያገኛል፡፡ በተጨማሪም የኦንላይን የገበያ መረጃ ይሰጣል፡፡

ከዚህ ሌላ ጽህፈት ቤቱ ኢትዮ-ሸማች በተሰኘ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመሰረታዊ ምርት ስርጭት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህም በህብረት ስራ ማህበራት ሱቅ አማካኝነት ምርቶች ለተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት ከ50 ሺህ በላይ የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በድግግሞሽ ተጠቃሚ መሆናቸውን ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

ከአገልግሎት አሰጣጡ ባለፈ 33 ሺህ የሚሆን የንግዱ ማህበረሰብን ማህደር ስካን በማድረግ በዲጂታል ተደራጅቶ ኦንላይን ገብቷል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ ማህደርን ሙሉ በሙሉ ከወረቀት ወደ ዲጂታል ለመቀየር እቅድ መያዙን አቶ በላይነህ አክለዋል፡፡

እንደኃላፊው ገለፃ፤ በፊት ንግድ ፈቃድ ለማውጣት፣ ለማደስና ሌሎችንም አገልግሎቶች ለማግኘት ነጋዴው ስራውን አቁሞ፣ ድርጅቱን ዘግቶ ወደ ተቋሙ መምጣት ይጠበቅበት ነበር፡፡ ሲመጣ ደግሞ ረዥም ሰልፍ ይዞ ነበር አገልግሎት የሚያገኘው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ባለበት ቦታ በኦንላይን አገልግሎቱን እያገኘ ነው። ይህም ጊዜና ጉልበትን እንዲቆጥብ አስችሏል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### በከተማ ግብርና ዘርፍ ለመሰማራት ማወቅ ያለብዎት ጉዳይ

በከተማ ግብርና ዘርፍ መሰማራት የሚፈልግ አካል የሚከተሉትን ጉዳዮች ማወቅ አለበት፡፡

1. በከተማ ግብርና ዘርፍ ከመሰማራት በፊት ስለሚሰማሩበት ዘርፍ እውቀት ሊኖር ይገባል፤
2. የአዲስ አበባ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፣ ከከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ ከተማ እና ወረዳ ደረጃ ድረስ የሚገኙ በመሆኑ ግንዛቤና የምክር አገልግሎት እንዲሁም ስልጠና በማግኘት ወደ ዘርፉ መሰማራት ይቻላል፣
3. በእንስሳት እርባታ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ በሌሎችም ዘርፎች ለመሰማራት እውቀትዎን ካዳበሩ በኋላ የሚሰማሩበትን ዘርፍ መለየትና መወሰን ይኖርብዎታል፤
4. የመስሪያ ካፒታል
5. የመስሪያ ቦታ፣
6. ለሚሰማሩበት ዘርፍ የሚሆን ግብአት የሚገኝበትን ቦታ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለአብነት የዶሮ እርባታ ላይ ከተሰማሩ ጫጩት ከየት ይገኛል፤ መኖና ሌሎችም፣ አጠቃላይ እውቀት፣ ካፒታል፣ የመስሪያ ቦታና ግብዓት ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህን አሟልቶ የተገኘ በዘርፉ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡ አለበለዚያ ካፒታል ስላለ ብቻ ስራውን መጀመር ለኪሳራ የሚዳርግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**የመረጃ ምንጭ** - የአዲስ አበባ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 87/2016 ተፈጻሚነት ወሰን፣ የከባድ ዲስፕሊን እና ቅጣት አወሳሰን

## ክፍል ሁለት

**በኪሩቤል አስናቀ (ዐቃቤ ህግ)**

ውድ አንባቢዎቻችን ባለፈው በክፍል አንድ ዕትማችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 87/2016 የአዋጁ ዓላማ፣ ተፈፃሚነት፣ የዲስፒሊን ቅጣት ሪከርድ አያያዝ፣ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣ ቅጣታቸው እና የሚያስከትሉት ጥፋቶችን በተመለከተ አስነብበናችኃል። የፅሁፋን ቀጣይ ክፍል እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ፡፡



### የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰን

ይህ ሁኔታ የተደነገገው በአዋጁ አንቀጽ 96 ሲሆን፤ በዚህ ድንጋጌ ስር ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መደበኛ የዲስፐሊን ምርመራ የሚያካሄድና የውሳኔ ሃሳብ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ የዲስፐሊን ኮሚቴ ማቋቋም ሲኖርበት፤

- ቅጣቱ የማንኛውንም ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፤
- ቅጣቱን በተመለከተም የዲስፐሊን ኮሚቴ አማካኝነት ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የቀረበለት የመንግስት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሃሳቡን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፤
- ኮሚቴው ከባድ የዲስፐሊን ጥፋት መፈፀሙን ካመነ በዲስፐሊን ኮሚቴው ውሳኔ ሃሳብ ላይ በራሱ ከመወሰን ይልቅ ከባድ የዲስፐሊን ጥፋት የፈጸመው ሠራተኛ ከሥራ የሚያሰናብተው ከሆነ ጉዳዩን ለመሥሪያ ቤቱ ስትራቴጂክ ካውንስል በማቅረብ ማስወሰን አለበት፤ ጉዳዩ የተፈጠረበት ቦታ ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ከሆነ በደረጃው ያለው ካቢኔ ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል፤
- ስትራቴጂክ ካውንስል ወይም በክፍለ ከተማ እና ወረዳ ካቢኔ አማካኝነት የተሰጠ ከሥራ የማሰናበት ውሳኔ በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ በተቋቋመ ማንኛውም አስተዳደራዊም ሆነ መደበኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታይ አይችልም፡፡

### የይርጋ ጊዜ

- ቀላል የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፐሊን ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ሆኖም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ያልወሰደው የሥራ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
- በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የወንጀሉን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፤
- በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የደንብ መተላለፍ ክስን ለማቅረብ በወንጀል ህጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፤

**ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም። ሆኖም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ያልወሰደው የሥራ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል**

- በዚህ አዋጅ መሰረት የዲስፐሊን ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜያት ቢኖሩም የዲስፐሊን ክስ ለማቅረብ ኃላፊነት ያለበት የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ክሱን ካላቀረበ በዲስፐሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፤
- ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ መብቶቹን ለሚመለከተው አካል በስድስት ወር ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

# የመዲናዋ ጎዳናዎች ትናንት እና ዛሬ

**በሄለን ጥላሁን**

ቀናችንን ስንጀምር “ሰላም አውለኝ፤ ከድንገተኛ ክስተት ታደገኝ” ብሎ እንደየ እምነታችን ፈጣሪን ለምኖ መውጣት መልካም ነው። ይህን ልንል የወደድነው በምክንያት ነው። ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት በማሽከርከር ሙያ ዘርፍ ተሰማርተው ይሰሩ የነበሩት አቶ ቴዎድሮስ ሰለሞን አዲስ አበባ ከተማ ላይ ሲያሽከረክሩ የገጠማቸውን ሳቅ እየቀደማቸው የተረኩልንን ስንሰማ አባባሉን ልብ እንድንለው ያስገድደናል፡፡

“ከዕለታት በአንዱ ቀን መኪናዬን እያሽከረከርኩ እያለ የተቦረቦረ አስፋልት ውስጥ ገባሁ፡፡ አስፋልቱ ያቆረው ውሃ በጭቃ የተሞላ ስለነበር ታክሲ ስትጠብቅ የነበረችውን የዘነጠች ወጣት ጭቃ አለበሳት፡፡” ሲሉ ገጠመኛቸውን የጀመሩት አቶ ቴዎድሮስ፣ በወቅቱ የወሰዱት እርምጃም እንደ አንዳንድ አሽከርካሪዎች ድርጊቱን ፈፅሞ በፍጥነት አካባቢውን ጥሎ መሄድ አልነበረም፡፡ ከሁሉም ያስቀደሙት መኪናቸውን ወደ ዳር በማቆም ይቅርታ መጠየቅን ነበር፡፡ ወጣቷን በተፈጠረው ድርጊት ይበልጡኑ እንድትበሳጭ ያደረጋት ምክንያት በወቅቱ ለስራ ቅጥር የቃለ መጠይቅ ፈተና ለመውሰድ ባላት ነገር ዘንጣ እየሄደች እያለች መሆኑን አብራርተዋል፡፡


ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ዘሪሁን ፃዲቅ፣ ወጣት አወቀ አረጋ እና አቶ ቴዎድሮስ ሰለሞን

ይህ ክስተት እንዴት እንደተፈጠረ አቶ ቴዎድሮስ ሲያስረዱም፤ ወጣቷ ጉዳዩን እንዲህ በቀላሉ ማለፍ ስላልወደደች የተበላሸባትን ልብስ በአዲስ እንዲቀየርላት ነበር የጠየቀችው፡፡ እርሳቸውም በወቅቱ የነበሩበት ድንጋጤ አይደለም ልብስ ሌላ የሚከሳትን ለማድረግ ፍቃደኛ ነበሩ። ያለችውንም አደረጉላት፡፡ ለስራ ቅጥር የነበራት መጠይቅ እንዴት እንደሆነ ለመስማት ስልክ በመለዋወጥ ነበር የተለያዩት፡፡ ታድያ በሚያናድደው ክስተት የተዋወቁት ግለሰቦች ደጋግመው በመደዋወል ህይወታቸውን ወደ ፍቅር መስመር ቀየሩት፡፡ ቤተሰብ መስርተው በመኖርም ደስተኛ ህይወት እያሳለፉ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

“በህይወታችን የሚገጥሙን ጉዳዮች የቱንም ያክል መጥፎ ቢሆኑም እንኳን መልካም ነገር ይዞ እንደሚመጣ ማሰብ ያስፈልጋል” የሚሉን አቶ ቴዎድሮስ የገጠማቸው መጥፎ አጋጣሚ ለመልካም እንደሆነላቸው ሲያስቡ እንደሚደሰቱ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም አዲስ አበባችን ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበራት የመንገድ ስርዓት በርካቶችን ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ የሚያደርግ ነበር፡፡ የመንገድ ጥበት፣ የተጎዱ አስፋልቶች እንዲሁም እግረኛው ከአሽከርካሪ እኩል እየተጋፉ መሄድ እምብዛም አዲስ ባልነበረባት ከተማ የኮሪደር ልማቱ ፍፁም ገፅታዋን በመቀየር አዲስ ገፅታ እንደለገሳት አብራርተዋል፡፡

በተለምዶ ጉርድ ሾላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በእግረኛ መንገድ ሲጓዙ ያገኘናቸው አቶ ዘሪሁን ፃዲቅ፤ አዲስ አበባ ከተማ ላይ መኖር ከጀመሩ በርካታ ጊዜያትን ያስቆጠሩ ሲሆን በስራ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተማዋን ጠንቅቀው ያውቋታል። ከዚህ

> “ከዕለታት በአንዱ ቀን መኪናዬን እያሽከረከርኩ እያለ የተቦረቦረ አስፋልት ውስጥ ገባሁ። አስፋልቱ ያቆረው ውሃ በጭቃ የተሞላ ስለነበር ታክሲ ስትጠብቅ የነበረችውን ወጣት ጭቃ አለበሳት”

ቀደም በአንዳንድ ዋና ዋና መንገዶች ጭምር አስነዋሪ ብሎም ቀንን የሚረብሽ ተግባር ይፈጸም እንደነበር የእሳቸውን ገጠመኝ በማሳያነት በማጣቀስ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡ በውሃ መጠጫ በተለምዶ ሃይላንድ በሚባሉት የፕላስቲክ ውሃ መያዣያዎች ውስጥ ሽንት በመሸናት በመንገድ አስፋልቶች ላይ የሚጥሉ ግለሰቦች አሉ፡፡ ይህንንም ተከትሎ መኪናዎች ሲረግጧቸው ሰው ላይ ይረጫሉ፡፡ በእርሳቸው ላይ የሆነውም ይኸው ነበር፡፡

አቶ ዘሪሁን በአስተያየታቸው፤ የቱንም ያክል ከተሞች ቢፀዱም እንኳን የፀዳ አስተሳሰብን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ “አንድ ሰው የሰራውን ምግብ የሚመገበው በንፁህ የመመገቢያ ሰሃን እንደሆነው ሁሉ ያማሩና ያሸበረቁ መንገዶች ላይ ቆሻሻ መጣልም የእግረኛውን የመንቀሳቀስ መብት እንደ መረበሽ ነው የሚቆጠረው” ብለዋል፡፡ ባደጉ ሀገራት እናየው የነበረውን የሰለጠነ የመንገድ ስርዓት እዚሁ ሀገራችን ላይ ሆኖ ስናየው በእጅጉ አስደስቶናል ብለዋል፡፡

የመንገድ መብራቶች ለአስፋልቶቹ የሰጡት መልካም ድባብ መንፈስን የሚያረጋጋ ብሎም ሰላምን የሚሰጥ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ዘሪሁን ከዚህ ቀደም አምሽተው የመስራት ልምድ ነበራቸው፡፡ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ከስራ ወደ ቤታቸው እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ወቅት ነበር፡፡ ሌቦች ጨለማን ተገን በማድረግ ስልካቸውን እና በኪሳቸው የነበረውን ገንዘብ የዘረፏቸው። ለዚህ እንደ ምክንያት የሚያነሱት የመንገድ ዳር መብራቶች ባለመኖራቸው ሌቦች ድፍረት እንዲያገኙ አድርጎቸዋል የሚለውን ነው፡፡ አሁን ግን ምሽቱም እንደ ቀን ስለደመቀ ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት እና 4፡00 ሰዓት እንቅስቃሴ ቢደረግ ማንም ዞር ብሎ አያይም፡፡ የመንገድ ላይ የደህንነት ካሜራዎች እግረኞች በጥንቃቄ እንዲጓዙ አሽከርካሪዎችም በአግባቡ የትራፊክ ህጎችን ተከትለው እንዲያሽከረክሩ አግዟል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ሰፋፊ የእግረኛ እና የብስክሌት መንገድ፣ ለአካል ጉዳተኞች የተለየ መንገድ መሰራቱ፣ ሰፋፊ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መዘጋጀታቸው የትራፊክ አደጋን በመቀነስ በእግረኛው፣ በአሽከርካሪው ብሎም በመንገድ ሃብት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ አይነተኛ መፍትሔ ነው ሲሉም አክለዋል።

ወጣት አወቀ አረጋ ይባላል፡፡ በተለምዶ ሲ ኤም ሲ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጀርባ በጭነት አገልግሎት ተሰማርቶ ይሰራል፡፡ “ያደጉ ሀገራት ከተሞቻቸውን መልሰው ያለማሉ፤ ያድሳሉ፡፡ አዲስ አበባም የዚያ በረከት ተቋዳሽ ስትሆን እንደማየት የሚያስደስት ነገር የለም፡፡ ከዚህ ቀደም መኪናዬን አቁሜ ስሄድ ስፖኪዮ (የሚኪናዬ የጎን መስታወት) ይሰረቅ ነበር፡፡ አሁን ግን ሰፋፊ እና ለማቆም ምቹ የሆኑ የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች መኖራቸው እፎይታን ፈጥረውልኛል” ብሏል፡፡

እንደ አንድ አሽከርካሪ ቦሎ ለማደስ የመኪና የቴክኒክ ምርመራ ይካሄዳል። እግር መንገድም ለመንገድ ፈንድ በሚል የተወሰነች ክፍያ ይከፈላል፡፡ ታድያ ይህ ክፍያ ለተጎዳው መንገድ መጠገኛ የሚውል ነው፡፡ ታድያ ለበርካታ ዓመታት የመንገዶችን ደህንነትን ለማስጠበቅ እምብዛም አልተሰራበትም። አሁን ግን ሰፋፊ የመኪና እንዲሁም የእግረኛ መንገዶች በስፋት ተሰርተዋል። ከዚያም በላይ ከሩቅ ሆነን ብናያቸው ብሎም ጥሩ ጊዜ ብናሳልፍባቸው ብለን ያሰብናቸውን መናፈሻዎች ከደጃፋችን እነሆ መባላችን እጅግ እድለኛ ያስብለናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደኔ ያለ በእድሜ ገፋ ያለ አዛውንት መንገድ ሲደክመው የሚያርፍበት፤ ጥሩ የእግር ጉዞ ማድረግ ሲፈልግ ወገቡን አረፍ የሚያደርግበት ስፍራ ያስፈልገዋል የሚሉት ደግሞ አቶ ተሾመ ባልቻ ናቸው። ነዋሪነታቸው ኮተቤ ዜሮ ሁለት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲሆን በብዛት የእግር መንገድ ጉዟቸውን የሚያደርጉት ከካራሎ ወደ ሰሚት በሚወስደው መንገድ ከሰዓት ከ11፡00 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ ደከም ሲላቸው በመንገድ ዳር በተዘጋጁ ወንበሮች አረፍ በማለት ከተክሎች የሚያገኙትን መልካም አየር እየሳቡ ጤናቸውን መጠበቅ የእለት ተዕለት ተግባራቸው እንደሆነ ነግረውናል፡፡

በዓለም በየዓመቱ ከ1 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በትራፊክ አደጋ እንደሚሞቱ የዓለም ጤና ድርጅት እ.ኤ.አ 2023 ያወጣው መረጃ ያሳያል፡፡ ከ50 ሚሊዮን በላይ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አዳጊ ሀገሮች ደግሞ ችግሩ የከፋ ነው፡፡ እንደ ሀገርም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ እየተከሰተ ያለው የትራፊክ አደጋ መንስኤ ከሆኑት ምክንያቶች ከግንባር ቀደምቶቹ ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል የእግረኛ እና የመኪና አስፋልቶች ጥበት፣ የመኪና አሽከርካሪና ሳይክል የሚነዱ ሰዎች መንገድ አለመለየት፣ የመንገድ ዳር መብራቶች በአግባቡ አገልግሎት አለመስጠት እና የደህንነት ካሜራዎች አለመኖራቸው ችግሩን የከፋ አድርጎት እንደነበር እሙን ነው፡፡ የኮሪደር ልማቱ ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ስላለው ደህንነቱን መጠበቅ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል እንላለን፡፡

# የመዲናዋ ኪነ-ጥበባዊ መሰናዶዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባለፉት ቀናት የተለያዩ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ቀርበዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች ተሰናድተዋል። ከእነዚህ መካከል የፊልም ምርቃት፣ የመጽሐፍት መረጃዎች፣ የሙዚቃ ዝግጅቶችና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

"ዝይን" የተሰኘ ስብስብ መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው፡፡ የደራሲ አለማየሁ ገላጋይ የቀደሙ ሦስት የድርሰት ሥራዎቹን በአንድ ቅጽ ሆነው ለንባብ እንደሚበቁም አሳውቋል፡፡ ደራሲው በማህበራዊ ትስስር ገጹ ላይ፣ "ዝይንን ዳጎስ ብላ ስመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ 'ለካ ሰርቻለሁ፣ የሀገሬ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ አለሁበት' የሚል ምስክርነት ለራሴ ተሰማኝ" በማለት አስፍሯል። "ዝይን" በፍቅር ሥም፣ ታለ እና ሐሰተኛው የተሰኙ ቀደምት የልብ ወለድ ድርሰቶቹን በአንድ ቅጽ የያዘ ነው ተብሏል፡፡

በሌላ መረጃ "የጫሙት ሸካ" የተሰኘው ልብ ወለድ መጽሐፍ ከረዥም ዓመታት በኋላ መልሶ ለንባብ በቃ፡፡ በጉራጌኛ ቋንቋ የተጻፈ የመጀመሪያ ልብወለድ ድርሰት የሆነውና በደራሲ ገብረየሱስ ኃይለማርያም የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ባሳለፍነው ሳምንት ለሁለተኛ ጊዜ ታትሞ ለንባብ በቅቷል፡፡ ለዓመታት ከገበያ ጠፍቶ የነበረው ይህ ልብ ወለድ መጽሐፍ በዋናነት በፍቅር ላይ ያተኩራል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## ፊልም

"ሶቤክ" የተሰኘ በድርጊት የተሞላ ልብ አንጠልጣይ ፊልም ሊመረቅ ነው፡፡ ተዋናይ ግሩም ኤርምያስ በተወነበትና በጄኢ 123 ስቱዲዮ ተዘጋጅቶ በሜሎክ ኢንተርቴመንት የቀረበው ይህ ፊልም የፊታችን ሰኞ ሐምሌ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ነው በብሔራዊ ቴአትር ቤት የሚመረቀው፡፡ በምረቃው ሥነ-ሥርዓት ላይ ታላላቅ የዘርፉ ባለሙያዎችና በርካታ የጥበብ አፍቃሪያን ይታደማሉ። ከነሐሴ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በተመረጡ ሲኒማ ቤቶች መታየት እንደሚጀምር ታውቋል፡፡

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ ከሚታዩ ቴአትሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። የቅርብ ሩቅ ቅዳሜ 8:30 ሰዓት፣ ባሎችና ሚስቶች ደግሞ 11:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ይታያሉ፡፡ እሁድ ደግሞ በ8:00 ሰዓት 12ቱ እንግዶች፤ 11:30 ሰዓት እምዬ ብረቷ በዚሁ ቴአትር ቤት ለታዳሚያን ይቀርባሉ፡፡ እንዲሁም በቀጣይ ቀናት ማለትም ማክሰኞ በ11:30 ሰዓት ሦስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11:30 የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ 11:30 ሸምጋይ፣ አርብ በ11:30 የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ ያለው ቁጥር በግራ በኩል ካለው ቁጥር ጋር እናባዛለን፡፡ እንዲሁም ከታች ያሉት ሁለቱ ቁጥሮች እናባዛለን፡፡ ከዚያ በኋላ አባዝተን ያገኘናቸው ሁለቱ ቁጥሮች ከላይ ከክቡ በስተቀኝ ካለው ቁጥር ጋር በመደመር ያገኘነው ውጤት የመሃለኛው ቁጥር መምጣት ይኖርበታል። የጥያቄው መልስ አሰራር፣ 6 X 7 = 42 / 12 X 3 = 36 ከዚያ በኋላ 42 + 36 + 11 = የመሃለኛው 89 ይመጣል፡፡ በዚህ መሰረት ትክክለኛው የጥያቄ መልስና አሰራሩ፣ 7 X 6 = 42 / 14 X 4 = 56 / 42 + 56 + 2 =100 ከዚህ አንጻር የጥያቄው መልስ 100 ይሆናል




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የጥበብ ጉልበት ለበጎ አድራጎት

በጊዜው አማረ

ዳሩ ምንድ ነው የህይወት ውሉ
መኖር ካልቻለ አንዱ ለሁሉ
ጥንትም ከድሮ የመጣ እውነት

መተባበር ነው የኛ ማንነት... ይላል በእሱባለው ይታየው፣ ሳሚ ዳን (ሳሙኤል ብርሐኑ)፣ ቤቲ ጂ (ብሩክታዊት ጌታሁን) እና ዳዊት ጽጌ የተሰራው ሙዚቃ፡፡ ይህን ህብረ ዝማሬ በርካቶች ያውቁታል፡፡ ሙዚቃውን ሲሰሙ ልባቸው ይነካል። ይራራል፡፡ ለሌላ ወገን መድረስ እንዳለባቸው ያስባሉ፡፡ ምክንያቱም ኪነ ጥበብ በተለይ ሙዚቃ አንዱ ለሌላው እንዲደርስ፣ በጎነት እንዲስፋፋ፣ መረዳዳት ባህል እንዲሆን ትልቅ ሚና አለው፡፡

ኪነ ጥበብ ማህበረሰቡን ማስተማርና ማዝናናትን ጨምሮ መረዳዳትን ባህል ለማድረግ የማይተካ ሚና አለው፡፡ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችም በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ ይሰማራሉ፡፡ ሌሎችን ለበጎ ተግባር ያነሳሳሉ፡፡ ያነቃቃሉ፡፡ ያስተምራሉ፡፡ ሙዚቀኛው በመዝፈን፣ ሰዓሊው በስዕል ስራው እና በማስተማር ለማህበረሰብ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

በሀገራችን በሙያቸው ከማገልገል አልፈው የኪነ ጥበብ ስራቸውን ለበጎ ፈቃድ አላማ የለገሱ የጥበብ ባለሙያዎች ብዙ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ ወቅቱ ክረምት ነው፡፡ ክረምት በሀገራችን በርካታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ይህንን መነሻ በማድረግ ኪነ ጥበብ በተለይ በጎ አድራጎትን ከማስተማር አንጻር ያለውን ፋይዳ እንደሚከተለው አዘጋጅቶታል፡፡

ኪነ ጥበብ የሰው ልጅ ስሜቱን፣ ሀሳቡንና ህልሙን የሚገልጽበት ጥንትም፣ ዛሬም ድረስ የዘለቀ ዘመናዊ መንገድ ነው። ሙዚቃ፣ ስዕል፣ ቴአትር፣ ግጥም እና ሌሎች የኪነ ጥበብ ዘርፎች የህብረተሰብን ነፍስ የሚያድሱና የሚያነቃቁ ናቸው። በጎ ፈቃድ አገልግሎት ደግሞ በራሳችን ፍላጎት ለሌሎች የምናደርገው በጎ ተግባር ሲሆን፣ ማህበረሰብን የሚያጠናክርና የጋራ እድገትን የሚያመጣ ምሰሶ ነው። እነዚህ ሁለት የሚመስሉ ነገሮች በጥልቀት ሲታዩ፣ እርስ በርስ የሚደጋገፉና ማህበራዊ ለውጥን የሚያፋጥኑ የማይነጣጠል ቁርኝት አላቸው። ምክንያቱም አርቲስቶች በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የኪነ ጥበብ ስራዎቻቸውን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፣ ድህነትን ታሪክ ማድረግ፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ ችግኝ መትከልን፣ ትምህርት፣ የአረጋዊያን ቤት እድሳትን የመሳሰሉ መርሃ ግብሮች ላይ ተሳትፎ እንዲጨምር በዘፈን ወይም ድራማ ህብረተሰቡን በማነቃነቅ ለለውጥ እንዲተጋ ያደርጋሉ። የኪነ ጥበብ ኃይል ስሜትን የመንካትና መልዕክትን ከቃል በላይ የማስተላለፍ አቅም ስላለው በቀላሉ በጎ ተጽእኖ መፍጠር ይችላል፡፡

የሃበሻ ኳየር መስራችና የኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢተው ዳዊት፣ "ኪነ ጥበብ ሌሎችን ከማስተማር፣ ከማነቃቃትና ከማስተባበር አቅሙ አንጻር በልኩ ያልተነገረለት እንዲሁም ያልተሰራበት ነው፡፡ ኪነ ጥበብ ትልቅ ሃይል ነው፡፡ ይህን



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአረንጓዴ አሻራ ዙሪያ ከተዘፈኑ ዘፈኖች መካከል የስንታየሁ በላይ ሙዚቃ አንዱ ነው

ሃይል ደግሞ ለበጎ አድራጎት ስራዎች፣ ለልማት፣ ለመተጋገዝና ቀና ለሆኑ ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፤ ለአለብነትም 'እኔ ነኝ ደራሽ ለወገኔ' የሚለውን የሙዚቃ ስራ መጥቀስ ይቻላል" ይላል፡፡

በእርግጥም ኢትዮጵያዊ አብሮነትን፣ መረዳዳት እና መተጋገዝን በብዙ የሙዚቃ ስራዎችና የኪነ ጥበብ ውጤቶች ተንጸባርቋል፡፡ ከላይ ከጠቀስነው ሙዚቃ የተወሰኑ ስንኞችን ስንመዝ፡-

ሰው እየረዳ በደግነቱ
ቁራሽ እንጀራ ለሌለው ቤቱ
መኖር ነው ያገር ሰው
ባህል እምነቱ
አንዱ ሲሞት ነው
ያንግዜ ሞቱ
እኔ ነኝ ደራሽ
ለወገኔ እኔ ነኝ
እሱ ነው እኔን
ሰው ያረገኝ ያቆመኝ...፡፡

በዓለም ላይ በርካታ የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች ገንዘብ ለማሰባሰብ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን ያዘጋጃሉ። የጥበብ ትርዒቶች፣ የሙዚቃ ኮንሰርቶች፣ የስዕል ሽያጭ እና የቴአትር ትዕይንቶች ለበጎ አድራጎት ስራዎች የገንዘብ ምንጭ ይሆናሉ። አርቲስቶችም በነጻ ተሳትፈው ለበጎነት ተግባር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ለምሳሌ፡- በሀገራችን በዚህ ወቅት የአረጋዊያን ቤት በስፋት የሚታደስበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ማለት ሙዚቀኞችና የሙዚቃ ባንዶች እንዲሁም የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች በአደባባዮችና በመዝናኛ ቦታዎች ስራዎቻቸውን በማቅረብ፣ ማህበረሰቡን በማነቃነቅ እና ለቤት እድሳት የሚውል ገንዘብ በመሰብሰብና አረጋዊያን ከክረምት ብርድና ፍሳሽ እፎይ እንዲሉ ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡

ሙዚቀኛ ቢተው እንደሚለው ለወገኑ ቀድሞ መድረስ ያለበት በቅርብ ያለ ወገኑ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- እኔ ነኝ ደራሽ ለወገኔ የሚለው ሙዚቃ ዘመን ተሻጋሪና በጎነትን በትክክል የሚገልጽ ነው፡፡

እኛም ሆነ ሌሎች ሙዚቀኞችና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መሰል ስራዎችን መስራት አለብን፡፡ ምክንያቱም ኪነ ጥበብ ትልቅ አቅም አለው፡፡ የሰዎችን ስሜት መግዛትና ተጽእኖ ማሳረፍ ይችላል። ይህንንም በኮሪደር ልማቱ በተሰሩ የመዝናኛ ስፍራዎች ሙዚቃ ስናቀርብ መታዘብ ችያለሁ ሲል ያክላል፡፡

ፒተር ታሪየስ የተባሉ የዘርፉ ባለሙያ እ.ኤ.አ በ2024 ከኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢተው ሃሳብ ጋር የሚቀራረብ ጽሑፍ ለንባብ አብቅተዋል፡፡ "ነን ፕሮፊት" በሚል ገጸ-ድር ላይ ያሳተሙት ይህ ጽሑፍ "Volunteering opportunities that bring out the artist in you" የሚል ርዕስ አለው፡፡

ጸሐፊው እንደሚሉት፣ ኪነ ጥበብ ማህበረሰብን ከማነቃቃትና ከማስተማር አንጻር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የሰዎችን አእምሮ ያድሳል፡፡ ያነቃቃል። ስለዚህ አርቲስቶች ኪነ ጥበብን በመጠቀም በበጎ ፈቃደኝነት ሌሎችን ለመርዳት መስራታቸው የሚያስደንቅ አይደለም። ምክንያቱም ኪነ ጥበብና ማህበረሰብ አብረው ነው የሚኖሩት፡፡ ጥበብና በጎ አድራጎት ደግሞ ሊነጣጠሉ አይችሉም። ስለዚህ በኪነ ጥበብ ማህበረሰብን ማገልገል፣ ራስን ማገልገል ነው፡፡

በእርግጥ አንዳንዶች ችግኝ መትከል፣ አረጋዊያንን መንከባከብ ግዴታ እንጂ እንደ በጎ አድራጎት መታየት የለበትም የሚሉ አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በፈቃደኝነት የምናከናውነው በጎ ስራ ነው ይላሉ። ይህንንም በማስረጽ የኪነ ጥበብ ድርሻ ትልቅ ነው፡፡ በተለያዩ ሀገራት አርቲስቶች ሙዚቃ በመጠቀም ለተጎዱ ወገኖች ይደርሳሉ፡፡ የአረጋዊያንን ቤት ያድሳሉ። የአካባቢ ጥበቃን ያበረታታሉ፡፡ የችግኝ ተከላ ስራዎችን ያስተዋውቃሉ፡፡ ማህበረሰቡን ይቀሰቅሳሉ፡፡ በእኛም ሀገር በቂ ነው ባይባልም መሰል ስራዎች ግን ተሰርተዋል፡፡ ወቅቱ ክረምትና የችግኝ ተከላ የሚካሄድበት ወቅት እንደመሆኑ የዛሬ 6 ዓመት በሀገራችን ኮሜዲያኖች ስለአረንጓዴ አሻራ ከተሰራው የማነቃቂያ ሙዚቃ ጥቂት ስንኞችን እንምዘዝ፡፡

በሰሜን በደቡብ
በምስራቅ በምዕራብ
መሐል ላይ ያላችሁ
የሀገሬ ልጆች እንዴት ከረማችሁ
እንደተለመደው መጥተናል መጥተናል
ቀልድ ብቻ አይደለም ችግኝም ይዘናል፡፡
እኔም እዚህ፤ አንተ እዚያ ጋ
ጮማ እየቆረጥን ስንበላ ስጋ
ዛፍ መትከል አንዘንጋ....
እህት አበባ አንችም የእኛ ብርቱ
ከዚህ የበለጠ እንዳይሆን ሙቀቱ
ዛፍ መትከል ላይ በርቱ፡፡

"በጎ ፈቃደኝነትን በተመለከተ ትምህርታዊ የኪነ ጥበብ ስራዎች ዋጋቸው እልፍ ነው፡፡ አርቲስቶች እራሳቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ወይም በማህበረሰብ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመሳተፍ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። አርቲስቶች ችሎታቸውን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲያውሉ፣ ሌሎችም በተለያዩ መንገዶች የበጎ ፈቃድ ስራ ላይ እንዲሳተፉ ያነሳሳሉ። ከዚህ አንጻር እኔም መቄዶንያ በመሄድ ተሳትፎ አድርጌያለሁ" ይላል ሙዚቀኛ ቢተው፡፡

ኪነ ጥበብ ሰዎች እንዲሰባሰቡና አብረው እንዲሰሩ ያነሳሳል። የኪነ ጥበብና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ትስስር የህብረተሰባችን ብሩህ ተስፋ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፡፡ ምክንያቱም ኪነ ጥበብን በመጠቀም የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ማጠናከር፣ ማህበራዊ ለውጥን ማፋጠንና የተሻለ ዓለም መፍጠር ይቻላል። የኪነ ጥበብን ኃይል ለበጎ ዓላማ በመጠቀም፣ የማህበረሰብን አኗኗር መለወጥና ዘላቂ ልማትን ማምጣት ይቻላል፡፡

ኪነ ጥበብ ማህበራዊ ጉዳዮችን እና ችግሮችን በግልፅ በማሳየት ሰዎች የበጎ ፈቃድ ስራ ያለውን አስፈላጊነት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ችግር የገጠማቸውን ሰዎች የሚያሳይ ልብ የሚነካ ሙዚቃ፣ ፎቶ ግራፍ ወይም ፊልም ቢሰራ ተመልካቾች በእነዚያ ሰዎች ጉዳይ እንዲነኩ እና የመርዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸው ያደርጋል። አንድ ሙዚቀኛ አቅመ ደካሞችን ስለመርዳት ወይም ተፈጥሮን ስለመጠበቅ ወይም ችግኝ ስለመትከል ዘፈን ሲያቀርብ፣ ሌሎች ሰዎች የተጎዱት ወገኖችን ለመርዳት፣ በችግኝ ተከላና በሌሎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ የጋራ ለውጥ እና እድገት ማምጣት ይቻላል፡፡

ንዋይ ደበበ፣ አረጋሃኝ ወራሽ እና ፀጋዬ እሸቱ በጋራ በሰሩት ዘፈን፡-

መተዛዘን ቢኖር መረዳዳት ቢኖር
መተሳሰብ ቢኖር ሁሉም ቢተባበር
ሰው ለሰው ቢፋቀር ሁሉም ቢተባበር
የት ይደረስ ነበር...ያሉትም ለዚሁ ነው።

በአጠቃላይ፣ ኪነ ጥበብ የበጎ ፈቃድ ስራን ለማበረታታት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ግንዛቤን በመፍጠር፣ አብሮነትን ከፍ በማድረግ፣ ተስፋን በመስጠት እና መድረክን በመፍጠር፣ ኪነ ጥበብ ማህበረሰቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባህል እንዲያደርግ ያግዛል። ስለዚህ መንግስታት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ግለሰቦች የዚህን ትስስር አስፈላጊነት ተረድተው በጋራ መስራት አለባቸው።

የጠዋት ፀሐይ

# ልጆች፤ የስፖርት ማዘውተሪያዎቹ ምን ስሜት ፈጠሩባችሁ?

**በለይላ መሀመድ**

ልጆችዬ፤ እንዴት ናችሁ? ለአንድ ዓመት የደከማችሁበት የትምህርት ውጤትስ ጥሩ ነው አይደል፡፡ አሁን የምንገኘው የክረምት ወቅት ነው፡፡ ይህን የእረፍት ጊዜ ከምታሳልፉባቸው መካከል ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ይገኙበታል። ከሰሞኑ በ11ዱም ክፍለ ከተሞች 122 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተሰርተው ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል። እነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የእናንተን ጥያቄዎች ከመመለስ፣ በአካልም በአዕምሮም ብቁ ዜጋ ሆናችሁ እንድታድጉ ከማድረግ አንጻር ትልቅ ጥቅም አላቸው፡፡ እኛም ተመርቀው አገልግሎት እየሰጡ ካሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መካከል በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ስሙ ፈለገ ዮርዳኖስ በሚባለው አካባቢ ተዘዋውረን ሲጫወቱ ያገኘናቸውን ህጻናት አነጋግረናቸው የፈጠረባቸውን ስሜት እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

አማኑኤል አሉላ እና ቅዱስ አዲሱ በቅርቡ በተመረቀው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ልምምድ ሲያደርጉ

ቅዱስ አዲሱ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 13 ዓመት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የምጫወተው እና የምወደውም ጨዋታ እግር ኳስ ነው፡፡ ከሌሎች የስፖርት አይነቶች እግር ኳስ ስጫወት ደስ ይለኛል፡፡ የዘንድሮው ክረምት ደስ የሚል ነው፡፡ ትምህርት እንደጨረስን የምንጫወትበት አገኘን። በዛ ላይ መጫወቻው ይመቻል። የድሮው ግን በየሰፈሩ በሚገኝ መንገድ እና አስፋልት ዳር ስለነበር እየወደቅን እንቆስል ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ስንጫወት ቆርቆሮ ትመታላችሁ እያሉ ትልልቅ ሰዎች ያባርሩን ነበር፡፡ በአጠቃላይ ለመጫወት እንቸገር ነበር። አሁን የተሰራልን ሜዳ ግን በነጻነት እንድንጫወት የሚያደርግ ነው፡፡

ሌላው የ13 ዓመት አዳጊው አማኑኤል አሉላ አሁን ላይ ስለተሰራላቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ምቹነት ከድሮው ጋር በማነጻጸር ገልጾልናል። ሁልጊዜ መጫወት የምፈልገው እግር ኳስ ነው። ድሮ ሰፈር ላይ ስጫወት በደንብ ተሯሩጬ ስለማልጫወት ደስ አይለኝም ነበር። ይህ ሜዳ ከመሰራቱ በፊት መንገድ ላይ ነበር እንጫወት የነበረው። ሰዎች ሲንቀሳቀሱ እናስቸግር ነበር፡፡ እኛም ጨዋታችንን አቋርጠን ለማሳለፍ እንቆም ነበር፡፡ አሁን ግን እንደፈለግኩ ሩጬ ስለምጫወት እግሬ አጠቃላይ ሰውነቴ ሁሉ ተፍታትቷል። እኔም ጓደኞቼም ደስ እያለን ነው የምንጫወተው። ሜዳው ለእይታም ደስ ይላል፡፡ በደንብ ተለማምደን ውጤታማ እንደምንሆንም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፈለገ ዮርዳኖስ አካባቢ በተሰራው የልጆች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ላይ አግኝተን ያነጋገርነው አሰልጣኝ ሰይፈ ደምሴ እንደገለጸው፤ እንዲህ አይነት ለህጻናት ምቹ የሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ተሰርተው ለአገልግሎት እንዲበቁ መደረጉ በስፖርቱ ዘርፍ የተሻለ ትውልድ ለማፍራት ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ "ትውልዱ እድለኛ ነው" ያለው አሰልጣኝ ሰይፈ ይህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ መሰራቱ ለልጆች በስፖርቱ ዘርፍ ከወዲሁ መነቃቃትን፣ ነገ ሀገርን የሚያስጠሩ ትውልዶችን ለመቅረጽ አቅም የሚፈጥር ነው። ልጆች በዚህ ምቹ በሆነ ሁኔታ ከልጅነታቸው ጀምሮ መጫወታቸው በአካልና በአዕምሮ የተነቃቁና የጎለበቱ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደስተኛ ሆነው ነው እየተጫወቱ ያሉት፡፡ ምንም አይነት መሰናከል ሳይኖርባቸው፣ ክህሎታቸውን አውጥተው እንዲጫወቱ ያግዛቸዋል፡፡

ይህ ከመሰራቱ በፊት ግን ልጆች ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ነበር ይጫወቱ የነበረው፡፡ ይህም ያላቸውን እምቅ ችሎታ ለማውጣትም ሆነ ለማዳበር አይችሉም ነበር፡፡ ህጻናት ራሳቸውን ሳይጠብቁ በተለይም ኮብል ስቶን እንዲሁም አስፋልት ዳር ላይ ይጫወቱ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ለልጆቹም ሆነ ለቤተሰብ ስጋት ሆኖ ቆይቷል ብለዋል።

ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የምታደርጉ ልጆች አካላዊ እና አዕምሮአዊ ጠቀሜታ እንደምታገኙ ተረድታችሁ ይኸንኑ ማድረጋችሁን አጠንክራችሁ ቀጥሉ። ሌሎቻችሁ ደግሞ በስፖርት ማዘውተሪያዎቹ ለመጠቀም ራሳችሁን ማዘጋጀት እንዳለባችሁ እየመከርን መልካም የእረፍት ጊዜ እንዲሆንላችሁም ተመኝተናል፡፡

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

ሲነገር ምላሽ የሚሰጥ ነገር ግን የማይናገር ምንድን ነው? መልሱ

**መልስ:-** ለ. የገደል ማሚቶ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ብዙ ቁልፎች ያሉት ነገር ግን አንድ መቆለፊያ የማይከፍተው ምንድን ነው?**

ሀ. ፒያኖ
ለ. ክራር
ሐ. ጊታር

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

ኢኮኖሚ

# የአዲስ ህይወት ምዕራፍ እርሾ

- **“ሴፍቲኔት ለብዙ ሠዎች ትልቅ ውለታ ውሏል”**

**የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች**

**በደረጀ ታደሰ**

የሠላሳ አምስት ዓመቷ ወይዘሮ ጤናዬ ተሰማ፤ ትላንትን በትዝታ፣ ነገን ደግሞ በተስፋ የሚመለከቱበት ጊዜ ላይ ተገኝተዋል፡፡ ሥራ ማጣት፣ ልጆችን ለብቻ ማሳደግ፣ በተደራራቢ ችግር ለአስከፊ ኑሮ መዳረግ፣ ጉልበትን፣ ዕውቀትን፣ ጊዜን ወደ ውጤት መቀየር የሚያስችልን ቀዳዳ መመልከት አለመቻል... ተደማምረው የወይዘሮዋ ትላንትና ላይ ተፅዕኖ ፈጥረው ለዓመታት ቆይተዋል፡፡ የሁሉ ነገር አሸናፊ ጊዜ ነውና፤ የከበባቸውን የችግር ክንብንብ ገላልጦ የመፍትሔ አቅጣጫን የሚያመላክት በከተማ አቀፍ ደረጃ የሚተገበር መርሃ ግብር በራቸውን አንኳኳ፤ “ሴፍቲኔት”። በራቸውን ከፍተው ተቀበሉት፡፡ ወይዘሮዋ፤ ከቤት ወደ አደባባይ፣ ከሥራ አጥነት ወደ ሠራተኛነት፣ የሠው እጅን ከመጠበቅ ራስን ወደ መቻል፣ ከተስፋ መቁረጥ ነገን የተሻለ ለማድረግ ወደ ማለም አሸጋገራቸው፡፡

ነዋሪነታቸው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የሆነው ወይዘሮ ጤናዬ፤ ያለአባት ለሚያሳድጓቸው ሁለት ልጆች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት አቅቷቸው ያሳለፏቸው ጊዜያት እንዲያበቁ የሴፍቲኔት መርሃ ግብር ትልቅ ውለታ እንደዋለላቸው ይናገራሉ። በዕደ ጥበብ ሥራ ላይ ተሠማርተዋል። የራሳቸው ፈጠራ የሆነው እና በክር (በጥለት) በመጠቀም በእጅ የሚያመርቷቸው የተለያዩ አልባሳት (ቀሚስ፣ ሹራብ፣ ኮፍያ)፣ ጫማ፣ ቦርሳ፣ የሳሎን ምንጣፍ እና የመሳሰሉ ምርቶችን ለተጠቃሚዎች እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

በሥራው ራሳቸውን ለውጠውበታል። የ10ኛ እና የ6ኛ ክፍል ተማሪ የሆኑት ሴት እና ወንድ ልጆቻቸውን በተሻለ ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አድርገዋል፡፡ ዕምቅ ዕውቀት እና የፈጠራ ጥበብን አቀናጅተው እየሠሩት ላለው ሥራ፤ ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የፈጠራ ሥራ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል፡፡ ዕውቀትና ችሎታቸውን ሳይደብቁ ብዙዎችን አሰልጥነዋል፡፡ ከሰልጣኞቻቸው መካከል በቁጥር ስድስት ለሚሆኑ ሴቶች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት እንደሌላው ሠርቶ አደር ሁሉ፤ ከሥራ ገበታቸው ርቀው በቤታቸው እንዲቆዩ ተገድደው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ፤ “ከቆጠባችሁት ግማሹን ለእለት ጉርሳችሁ ማሟያ ይሁናችሁ” ተብሎ በሴፍቲኔት መርሃ ግብር ታቅፈው ለነበሩ የከተማዋ ነዋሪዎች ተሰጥቷቸው ነበር። ሁሉም በሚባል ደረጃ የተሰጣቸውን ገንዘብ ለተባሉት ዓላማ ሲያውሉ፤ ዕምቅ ችሎታቸውን ወደተግባር ለመቀየር ጊዜና ሁኔታ ሲጠባበቁ የነበሩት ወይዘሮ ጤናዬ፤ በተሰጣቸው ገንዘብ በሙሉ የተለያየ ቀለም ያላቸውን ክር (ጥለት) ገዝተው ወደ ቤታቸው ገቡ፡፡

ያንን ሁኔታ ያስታወሱት፤ “ከቆጠብነው ገንዘብ ውስጥ ግማሽ ተሰጠን፡፡ ለእኔ 3 ሺህ ብር ደረሰኝ፡፡ ሁሉም ጓደኞቼ በተሰጣቸው ብር አስቤዛ ሸመቱበት፡፡ እኔ ደግሞ ክር ገዝቼ ገባሁ፡፡ በክሮቹም ቆንጆ ቦርሳ እና ጫማ ሠራሁ፡፡ እግዚያብሔር እረድቶኝ የሠራኋቸው ወዲያው ተሸጡ። እጥፍም አተረፍኩባቸው፡፡ በድፍረት የጀመርኩት ሙከራዬ በሥራ ለመለወጥ የሚያስችለኝን ያልተጠቀምኩበትን አቅም እንዳውቅ ምልክት ሰጠኝ፡፡ ጅምሬንም ማጠናከሬን ቀጠልኩ” በማለት ነበር፡፡

“ሙያውን ከእናቴ ነው የተማርኩት። እናቴ ዳንቴል ትሠራ ነበር፡፡ በልጅነቴ እሷ ስትሠራ እመለከትም፤ እሞክርም ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም ዓይነት ስልጠና አልወሰድኩም፡፡" የሚሉት የክር ጠበብቷ፤ “ከሴፍቲኔት ስመረቅ 20 ሺህ ብር ይዤ ወጣሁ፡፡ ይህንን ብር ለመቀበል ተያዥ የሚጠየቅ ቢሆንም፤ ቀደም ብዬ ባሳየሁት የግል ጥረት የተደሰቱ የመርሃ ግብሩ አስተባባሪዎች፤ ያለምንም ተያዥ ገንዘቡን ፈቀዱልኝ፡፡ እኔም በተቀበልኩት ገንዘብ ክር፣ የጫማ ሶል እና አስፈላጊ ግብዓቶች ገዛሁበት፡፡ የተለያዩ ምርቶችን ማምረትና ለገበያ ማቅረቤን ቀጠልኩበት። ምርቶቼ ተፈላጊነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨመረ፡፡ በቤት ውስጥ የማዘጋጃቸውን ምርቶች በባዛር እና ኤግዚቢሽኖች ላይ የማሳየትና የመሸጥ ዕድል አገኘሁ፡፡ ደንበኞቼ እየበዙ መጡ፡፡ በአካባቢዬም የምሠራበትና የምሸጥበት አነስተኛ ሱቅ ተሰጠኝ፡፡ እነዚህ የመንግስት መልካም ድጋፎች ለተሻለ ስኬት የሚያበቃኝን ጉዞ አፋጠኑልኝ፡፡"

እንደ ወይዘሮ ጤናዬ ሁሉ በሴፍቲኔት መርሃ ግብር ተደራጅተው ራሳቸውን ከለወጡ እና ለሌሎች ምሳሌ መሆን ከቻሉ ነበዛዝት መካከል የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ነዋሪዋ ወይዘሮ ሞላሽ አሠፋ ሌላኛዋ ናቸው፡፡ በመርሃ ግብሩ ከመሳተፋቸው በፊት የዕለት ጉርሳቸውን ለማሟላት ይከብዳቸው እንደነበር ያስታወሱት እኚህ ወይዘሮ፤ "በሴፍቲኔት ከተካተትኩ በኋላ የሚያስፈልገኝን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት የምችልበትን ገቢ ወደ ማግኘት ገብቻለሁ፡፡ ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን ቁጠባም በመደበኛነት ስቆጥብ ቆይቻለሁ። ቁጠባው በመጨረሻ ለሥራ ማስኬጃ የሚውል ሲሆን፤ እኔ ከዚያ በፊት በየጊዜው ከማገኘው ገቢ በማስቀመጥ የራሴን ሥራ መጀመር ችያለሁ፡፡ ለልጄም ከትምህርቷ ጎን ለጎን የሕትመት ሥራ ላይ እንድትሰማራ አድርጌያለሁ፡፡" በማለት በመርሃ ግብሩ መታቀፋቸው ቀድመው ገቢ ማስገኘት ከሚችሉ አዳዲስ ሥራዎች ጋር መተዋወቅ መቻላቸውን ያስረዳሉ፡፡

በሴፍቲኔት መርሃ ግብር የሚጠበቅባቸውን ቆይታ ካጠናቀቁ በኋላ የቁጠባ ገንዘባቸውን ተቀብለው የሙሉ ጊዜ ሥራ የጀመሩ ሲሆን፤ ስለ ሥራው ዓይነት እና ተያያዥ ጉዳዮች በተመለከተ፤ “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለምዶ 18 ቁጥር ማዞሪያ በሚባለው አካባቢ ተገንብቶ ለአገልግሎት በበቃው ሼድ የመሥሪያ ቦታ ተሰጥቶኝ በሕትመት ሥራ (የአልባሳት፣ ባነር...) ላይ ተሰማርቻለሁ፡፡ በዚህ ሥራ ላይ ከተሰማራሁ አንድ ዓመት ከስድስት ወራት አካባቢ ሆኖኛል፡፡ አሁን ላይ የተሻለ ሥራ ለመሥራት በማሰብ የዘርፍ ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል የሥራ ዕቅድ አዘጋጅቼ ይህን ተፈጻሚ ለሚያደርገው አካል አስገብቻለሁ። የመረጥኩት ዘርፍ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ሲሆን፤ በዚህ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችለኝ ሕጋዊ ፈቃድ እንደተሠጠኝ የምገባበት ይሆናል።” ብለዋል

የምግብ ዋስትና (የሴፍቲኔት) መርሃ ግብር ከከፋ ድህነት ለመውጣት፣ ራስን ከአዳዲስ ሥራዎች ጋር ለማስተዋወቅ፣ ለራስ እና ለሌሎች የሚጠቅም ሥራ ፈጣሪ ሆኖ ለመገኘት የሚያስችል እና ያስቻለ ስለመሆኑ በመዲናችን በርካታ ሕያው ምስክሮች አሉ። የወይዘሮ ጤናዬ እና የወይዘሮ ሞላሽ ተሞክሮም ይህንን ነው የሚያሳየን። የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች በየጊዜው ራሳቸውን በዕውቀት እና ክህሎት ለማብቃት የተለያዩ አማራጮችን የሚጠቀሙ መሆናቸው በፈጣን ለውጥ ውስጥ በሚጓዘው ዓለም ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችላቸዋል።

ለዚህም ነው፤ ወይዘሮ ሞላሽ በሴፍቲኔት መርሃ ግብር ከታቀፉ በኋላ ያቆሙትን ትምህርት ወደ መከታተል የገቡት። ለትምህርት ያላቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሄዱበትን ርቀትና ውጤት እንደሚከተለው ያብራራሉ፤ “እኔ ትምህርቴን ተምሬበታለሁ። በ2015 የትምህርት ዘመን በአካውንቲንግ ዲፕሎማ ይዣለሁ፡፡ አሁን ላይ በሕዝብ አስተዳደር የድግሪ ትምህርት እየተከታተልኩ ነው። ይህን ማድረጌ ሥራዬን በዕውቀት እንድመራ አቅም ይሆነኛል። ለሌሎችም ምሳሌ መሆን እችላለሁ፡፡"

በርካቶችን ተጠቃሚ ያደረገው የሴፍቲኔት መርሃ ግብር እንደከተማ አስተዳደር አበረታች ስኬት የተመዘገበበት ዘርፍ ስለመሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል። የመርሃ ግብሩ ጠቀሜታ፤ ተቋማት በሪፖርታቸው በሚገልፁት አሃዛዊ መረጃ ብቻ የተወሰነ አይደለም። መርሃ ግብሩ መሥራት የሚችሉ ዜጎችን በከተማዋ ልማት ሥራ ላይ በማሳተፍ በዘላቂነት የራሳቸውን ሥራ የሚፈጥሩበትን ሁኔታ የሚያመቻች በመሆኑ፤ የመጠቀምና ያለመጠቀም ውሳኔ በተሳታፊ ዜጎች እጅ ያለ ነው፡፡



ፎቶ- ከፋይል

በወ/ሮ ጤናዬ ተሰማ ፈጠራ ታክሎባቸው ለተጠቃሚዎች ከሚቀርቡ ምርቶች በከፊል

ይህንን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች የሚከተለውን አስተያየት እና ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል፤ “የምግብ ዋስትና (የሴፍቲኔት) መርሃ ግብር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ መርሃ ግብሩ ለተጠቀመበት በጣም ጥሩ ነው። የተጠቃሚው አስተሳሰብ ግን ወሳኝ ነው።

ተጠቃሚው ነገ እለወጥበታለሁ ብሎ ካሰበ እና ለመለወጥ የሚያስችለውን ሥራ ቀድሞ ከሠራ ይለወጣል፡፡ ሴፍቲኔት ለብዙ ሠዎች ትልቅ ውለታ ውሏል። አካባቢን አፅድቶ፤ ዳቦ መብላት የሚቻልበትን ዕድል ፈጥሯል፡፡ ከዕለት ጉርስ ማሟላት ባለፈ በመጨረሻ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የራስን ጥረት ይጠይቃል፡፡

ከሥራ ማጣት ወደ ሥራ ፈጣሪነት፣ ከዕለት ጉርስ መሸፈን ወደ ሌሎች አለኝታነት፣ በዛሬ ስኬት ላይ ከመወሰን ወደ ተሻለ የስኬት ማማ መዳረሻነት እንደ እርሾ ሆኖ አለመጠቀማቸው ምስክርነት የሰጡት ጀግኒቶች ነገ እናሳካዋለን ብለው ስላቀዱት የሥራ ውጥን ነግረውናል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# በአንድ ጠጠር ብዙ ወፍ

- **ቁጥራቸው ከ6 መቶ በላይ የሚሆኑ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የከተማ ግብርና ስራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ**

**በሄለን ጥላሁን**



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በደጃዝማች ወንድይራድ ቅድመ መጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና ስራዎች በከፊል

ከተመሰረተ ስምንት አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል፤ እድሜ ጠገቡ የደጃዝማች ወንድይራድ ቅድመ መጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። በተንጣለለው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከማለዳው 1፡00 ሰዓት ላይ ተገኝተናል፡፡ ገና እግራችን ቅጥር ግቢውን እንደረገጠ አይናችን አትክልቱ ስፍራ ላይ አረፈ። አካባቢው ላይ ያለውን ውብ ተፈጥሮ አለማድነቅ አይቻልም፡፡ በመማሪያ እንዲሁም በተለያዩ የስራ ክፍሎች አካባቢ የውበት አበቦች ተተክለዋል። ዘወር ብሎ ደግሞ ሸቅብና አግድም የከተማ ግብርና ስራዎች በስፋት እና በልዩ ጥንቃቄ ተተክለዋል፡፡ የአትክልት ሥፍራው አቀማመጥ፣ ዓይነተ ብዙነት እና ውበት ለትምህርት ተቋሙ ቅጥር ግቢ ልዩ ገፅታን አላብሶታል፡፡ የእነዚህ ድምር ውጤት በቦታው ለተገኘ ሠው የመንፈስ ደስታ እና እረፍትን ያጎናፅፋል፡፡

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ክቤ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ቀደም ሲል የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በአረምና በቁጥቋጦ የተዋጠ ነበር፡፡ ይህም የቅጥረ ግቢውን ገፅታ ከማበላሸቱ በተጨማሪ፤ ለመማር ማስተማር ሂደቱ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ይሁን እንጂ፤ በመላው ሀገሪቱ የከተማ ግብርና መርሃ ግብር በይፋ እንዲጀመር መደረጉን ተከትሎ ትምህርት ቤቱ የራሱን የተቀናጀ የከተማ ግብርና ከነባራዊው ሁኔታ እና ካለው ፀጋ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ አቅዶ መተግበር ጀምሯል፡፡ በሥራው ላይም ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም የተማሪ ወላጆች እንዲሳተፉበት ተደርጓል፡፡ በዚህም እንደ ቆስጣ፣ ካሮት፣ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ቲማቲም፣ አቮካዶ፣ ፓፓዬ እና መሰል አትክልቶችን ማልማት ተችሏል። በእንሰሳት እርባታ መስክም፡- ዶሮ፣ የወተት ላሞች፣ በጎች እና ፍየሎችን የማርባት እና የማድለብ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተጨማሪም ንቦችን የማነብ እና ማር የማምረት ሥራ ትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ስራ አንድ አካል ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በንቃት እንዲሳተፍበት እየተደረገ ባለው የከተማ ግብርና መርሃ ግብር ውጤታማ ስራ መስራት የተቻለበትን ምክንያት በዋናነት ተማሪዎች በእርሻ ትምህርት ንድፈ ሃሳቡን ከተማሩ በኋላ በተግባር መከወን መቻላቸው የሚለው ቀዳሚው መሆኑን አቶ ሰለሞን ነግረውናል። አያይዘውም ተማሪዎች የተማሩትን የንድፈ ሃሳብ ዕውቀት ወደ ተግባር ለውጠውት ውጤቱን ጭምር በግልፅ ማየት መቻላቸው የከተማ ግብርናን የበለጠ እንዲወዱት እና እንዲተገብሩት አስችሏቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከከተማ ግብርና የሚገኘውን ትኩስ የጓሮ አትክልት እና እንቁላል ለትምህርት ቤቱ ምገባ ማዕከል በግብዓትነት መጠቀም ተችሏል። ይህ በማዕከሉ የሚሰሩ እናቶች ጤናማ ምግቦችን አዘጋጅተው ለተማሪዎች ማቅረብ እንዲችሉ አቅም ፈጥሯል ብለዋል፡፡

በትምህርት ቤቱ የ6ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ሮቤል ታረቀኝ፤ በእረፍት ጊዜው እንደ ቆስጣ እና ድንች ያሉ የጓሮ አትክልቶችን በመኮትኮት እንደሚንከባከብ፣ ይህንን ስራ በትምህርት ቤቱ ብቻ ሳይሆን በመኖሪያ ቤቱ ጭምር እንደሚተገብረው ጠቁሞናል፡፡ ይህንን መነሳሳት ያገኘው በትምህርት ቤቱ መምህራን አማካኝነት ተክሎችን እንዴት በቀላሉ አፅድቆ መጠቀም እንደሚቻል በቀላል ማየት በመቻሉ እንደሆነ ተናግሯል፡፡

የኢትዮጵያ እድገት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህርት ወይዘሮ መቅደስ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ድሮ ድሮ ልጆች አትክልቶችን ሲያበላሹ እና ሲያጠፉ ነበር የምናውቀው፡፡ አሁን ግን ስለ እፅዋት አስፈላጊነት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለያየ የማስተማሪያ መንገድ በመጠቀም ተማሪዎች ላይ ሰፊ ሥራ ትምህርት ቤቱ መሥራት መቻሉን አብራርተዋል፡፡

የአካባቢ ፅዳትን በአግባቡ መጠበቅ የእለት ተእለት ተግባሩ ያደረገው የኢትዮጵያ እድገት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ስለቆስጣ፣ ጎመን፣ ካሮት እና ድንች የመሳሰሉትን የጓሮ አትክልቶች በቂ እውቀት በመስጠት ወደ ስራ መገባቱን አስረድተዋል፡፡ በመላው ሀገራችን እየተተገበረ የሚገኘው የከተማ ግብርና ስራ የትምህርት ቤቶችን በር በማንኳኳት አሁን ላይ ከጓሮ አትክልት የሚገኘው ምርት ለተማሪዎች ምገባ ጭምር እየዋለ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች በእርሻ ትምህርት ከሚያገኙት እውቀት ባሻገር በተግባር እንዴት ስራ ላይ ይውላል? የሚለውን እንዲያዩ ያግዛቸዋል ሲሉም አክለዋል፡፡

ሀና ገዛኸኝ የትምህርት ቤቱ ተማሪ ናት፡፡ በትምህርት ቤቱ ግቢ የተተከሉትን አትክልቶች ውሃ እያጠጣች ትንከባከባለች፡፡ ይህንን የምታደርግበትን ምክንያት ስታስረዳ፣ በንፁህ አካባቢ የተተከሉ አትክልቶችን ለምግብነት ማዋል ለጤና ተስማሚ መሆኑን በመረዳት ነው፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ተክሎች በቂ ውሃ ካገኙ የምግብ ይዘታቸው የተሻለ እንደሚሆን ከተማረችው ትምህርት እውቀት ጨብጣለች፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በቤቷ ጭምር ቆስጣ እና ካሮት በመትከል እያሳደገች ትገኛለች።

ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ትምህርት ቤቶች በማሳያነት ጠቀስን እንጂ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ባላቸው ክፍት ቦታ እየሰሩት ያለው የከተማ ግብርና ይበል የሚያሰኝ እና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ሚና አይተኬ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የከተማ ግብርና ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ፋሩቅ ጀማል ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ቁጥራቸው ከ6 መቶ በላይ የሚሆኑ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የከተማ ግብርና ስራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተማሪዎች ምገባ ያለ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የእርሻ ትምህርት ይሰጣል፡፡ በዚህ አማካኝነት ተማሪዎች ስለ እፅዋት በቂ እውቀት በትምህርት ካገኙ በኋላ በተግባር ደግሞ እንዴት ይተገበራል? የሚለውን ግንዛቤ ለመፍጠር አስችሏል፡፡

የከተማ ግብርና ስራውን በስፋት እና በተጠናከረ መልኩ መተግበር የተፈለገበትን ምክንያት ኮሚሽነሩ አቶ ፋሩቅ እንደገለጹት፤ ትምህርት ቤቶች የምርት ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል፣ የከተማ ግብርና ስራዎች እንዴት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መተግበር እንዳለባቸው ለከተማዋ ነዋሪ ህብረተሰብ ለማስረፅ እና ለማስተግበር በማስፈለጉ እንዲሁም በሚያመርቷቸው ምርቶች ተጠቅመው በምገባ እራሳቸውን ለማስቻል የሚል አቋም በመያዝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው የሚያዩትን ወደ ቤታቸው ጭምር እንዲተገብሩት ጥሩ መነቃቃትን ይፈጥራል የሚል እምነት በማንገብ መገባቱን አንስተዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በተሰራው ስራ የተገኘውን ውጤት ኮሚሽነሩ ሲያስረዱ፣ የከተማ ግብርና ስራዎችን በትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ባሻገር ተማሪዎች እንደ አንድ የስራ ባህል አድርገው እንዲረዱት ማድረግ ተችሏል፡፡ በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከባለድርሻ አካላት በተለይም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ ለትምህርት ቤቶች በቂ የዘር አቅርቦት በመስጠት፣ የሙያ ድጋፍ በማድረግ የቅርብ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ገልፀዋል፡፡

ከምንም በላይ ልጆች ላይ የሚሰራው ስራ ቀጣይነት ያለውና ትውልድን አሻጋሪ መሆን አለበት የሚል እምነት በማንገብ ቃልን በተግባር ለማሳየት ተችሏል የሚሉት አቶ ፋሩቅ፣ መዲናችን አዲስ አበባም የከተማ ግብርና ስራዎችን በስፋት መከወን መቻሏ የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥና የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርዓት እንዲኖር ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

**የከተማ ግብርና ስራውን በስፋት እና በተጠናከረ መልኩ መተግበር ከተፈለገባቸው ምክንያቶች አንዱ ትምህርት ቤቶችን የምርት ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል ነው**

## “በምክክር...

ከገጽ 7 የዞረ

### ኮሚሽኑ ምን እየሰራ ነው?

የግጭት ወይም ጦርነት መኖር ሶስት ችግሮችን ያስከትላል፡፡ በሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት፣ ከፍ ሲል የሕይወት መጥፋትና በአጠቃላይ የአዕምሮ ስብራት ያመጣል የሚሉት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር)፣ ኮሚሽኑ ከመነሻው የተዘነጉ ወይም ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች በሀገራዊ ምክክሩ ሂደት ውስጥ ዋና ተሳታፊ እንዲሆኑ መርሁ አድርጎ ነው የተነሳው፡፡ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም አካታችና አሳታፊ እንዲሆን ተቀምጧል፡፡ በዚህም መነሻ አካል ጉዳተኞች ከተወከሉበት ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረምና ግንኙነቱን በማጠናከር ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ አካል ጉዳተኞች እንዲሳተፉ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን አንስተዋል፡፡

በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱም፤ “አጀንዳዎቻችን ናቸው” የሚሏቸውን በፌዴሬሽናቸው አማካኝነት አቅርበዋል። በቅርቡም መስማት ከተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ማህበር የቀረቡ አጀንዳዎችን ኮሚሽኑ ተቀብሏል፡፡ ዓይነ ስውራንና የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው በሂደቱ እየተሳተፉ ነው። አንዳንድ “አልተካተትንም” ብለው የሚያስቡ ካሉም አሁንም አጀንዳዎችን እንደሚቀበል ጠቁመዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች ያሉባቸው ፈተናዎች ብዙ ናቸው፡፡ በመንገድ፣ በትራንስፖርት፣ በህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በሌሎችም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ መብት የተሰጣቸው ቢሆንም በትግበራ ላይ ብዙ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ግጭት ሲኖር የበለጠ ተገጂ ከሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል አካል ጉዳተኞች እንደሚጠቀሱ ያነሱት መስፍን (ፐ/ር)፣ በምክክሩ ሂደት ተሳታፊነታቸውን ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

### ቀጣይ ምን ይጠበቃል?

መስፍን (ፕ/ር) እንደሚሉት፣ ምክክር ማለት በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ወይም ብዙዎች አስቀድመው ወስነው መጥተው የራሳቸውን አጀንዳ ብቻ የሚያፀድቁበት አይደለም፡፡ ምክክር በሚገባ በመከባበርና በመደማመጥ ተነጋግሮ የጋራ አጀንዳዎች ወደፊት የሚመጡበትና መግባባት ላይ የሚደረስበት ሂደት ነው፡፡ መግባባት ላይ የማይደረስባቸው ጉዳዮች ካሉም ጊዜ በመስጠት በቀጣይነት በህዝበ ውሳኔ ወይም በሌላ መንገድ ወሳኔ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል፡፡

መመካከር አጀንዳ መስጠት ብቻ ሳይሆን ስለ አጀንዳው ጥልቅ የሆነ እውቀት መያዝን ይፈልጋል፡፡ እውቀት የሚያስፈልገውም ምክንያታዊ ለመሆን ነው፡፡ ተሳታፊዎች ከወዲሁ በመከባበር፣ በመደማመጥ ተነጋግሮ ወደ መግባባት ለመምጣት ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ መገናኛ ብዙሃን ህዝቦች ተካባብረው ለመደማመጥና ለመነጋገር እንዲችሉ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መስፍን (ፐ/ር) ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዓይነ ስውራን ማህበር ፕሬዝዳንት አቶ አበራም ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ከእያንዳንዱ ግለሰብ፣ ማህበረሰብና የፖለቲካ ተዋናዮች ሆደ ሰፊነት፣ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርን ማሰብ ይጠይቃል፡፡ ኢትዮጵያ የምትገነባው በመቀበል ብቻ ሳይሆን በመስጠትም እንደሆነ መረዳት ይገባል፡፡

ሁላችንም በሰላም ወጥተን፣ ሰርተን፣ በሰላም የምንገባባትና የምንኖርባት ኢትዮጵያን ከፈለግን በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ይኖርብናል፡፡ በመሰረታዊ ልዩነቶቻችን ላይ መግባባት ከፈጠርን ሌሎች ጥያቄዎችን እየፈቱ መሄዱ ቀላል እንደሆነ አቶ አበራ ያስገነዝባሉ፡፡

“ሰላምን ቅድሚያ የምንሰጠው ስለሆነ በየትኛውም አካል ሰላም ለማምጣት የሚደረግ አጀንዳ ላይ እንሳተፋለን፡፡ ” የሚሉት አቶ ታደሰም፣ በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላምና እድገት ለማረጋገጥ ልዩነቶችን በውይይትና ምክክር መፍታት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ ለሀገራችን ህመም ፈውስ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ሁሉም አካላት ዕድሉን በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን በምክክሩ ሂደት የሚያደርገውን ተሳትፎ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክር ኢትዮጵያ ከገባችበት የግጭት አዙሪት ለማውጣት ሁነኛው መንገድ ነው፡፡ የምክክሩ ሂደትና ውጤት በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ ሲሆን በተለይ ደግሞ የችግሮች ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ለሆኑ አካል ጉዳተኞች እየተንከባለሉ የመጡ ችግሮችን የሚፈታና ነገን በተስፋ እንዲጠብቁ የሚያደርግ ነው፡፡

## አገልግሎቱ...

ከገጽ 9 የዞረ

በ2017 በጀት ዓመት ከተፈቀደላቸው ውጪ ሌላ የይለፍ ቃል በመክፈት በኦንላይን መደበኛ ያልሆነ አገልግሎት ሲሰጡ የተገኙ 4 ባለሙያዎች በመለየት ደመወዝ የመቁረጥ፣ እንዲሁም የቃልና የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተወሰደም ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለህብረተሰቡ ሊደርስ የነበረውን ዘይትና ስኳር ከታለመለት ዓላማ ውጪ በማዋል ለነጋዴ የሸጡ 7 የህብረት ስራ ማህበራት የሽማች ባለሙያዎች የተለዩ ሲሆን 5 ባለሙያዎች ከስራ ሲታገዱ፤ 2 ባለሙያዎች ከስራ ገበታቸው እንዲሰናበቱ መደረጉን አቶ በላይነህ ገልፀዋል፡፡

አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ የመስጠት ስራውን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የንግድ ፈቃድ ያላደሱ እንዲያድሱ የማድረግ፤ ያለ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩ ነጋዴዎችን ወደ ህጋዊ መስመር የማስገባት ስራውን በትኩረት በመተግበር ለተገልጋዩ ህብረተሰብና ለነጋዴው ቀልጣፋ አገልግሎት የመስጠት ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ በላይነህ ጠቁመዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉ በሁለቱም ክፍለ ከተሞች ባደረገው ቅኝት ቀድሞ እንደነበረው አገልግሎት ለማግኘት ሰልፍ አይታይም፡፡ የተወሰኑ ተገልጋዮች ተቀምጠው ሲገለገሉ ተመልክተናል። ይህ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ መደገፉ ያስገኘው ውጤት እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅም ይኼንኑ የሚያጠናክር ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ኃላፊዋ እንዳብራሩት፣ በቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በ2013 ዓ.ም ሲሆን ቢሮው በሁለት ዘርፎች ማለትም በቁጥጥር እና የንግድ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ዘርፍ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። በቁጥጥር ዘርፉ ያለ ንግድ ፈቃድ የሚነግዱ፣ በተሰረዘና በታገደ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩ፣ ንግድ ፈቃድ ሳያድሱ የሚሰሩ፣ ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶችን የሚይዙ፣ ሚዛን አጉድለው የሚሸጡትንና ሌሎችንም የመከታተልና የመቆጣጠር ስራው በሲስተም በመታገዝ እየተሰራ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የንግዱ ማህበረሰብ አገልግሎቶችን በስልኩ በኦንላይን እያገኘ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ችግር ካጋጠመ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ስራው በቢሮው ሙሉ በሙሉ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የንግድ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት አገልግሎት ዘርፍ ከ19 አገልግሎቶች 16ቱ በኦንላይን ነው የሚሰጡት። ለአብነት የንግዱ ማህበረሰብ አዲስ ንግድ ፈቃድ ማውጣት፣ ንግድ ፈቃድ ማደስ፣ ንግድ ምዝገባ፣ ንግድ ፈቃድ መመለስ፣ ካፒታል ማሳደግና ሌሎችን አገልግሎቶች በኦንላይን ያገኛል፡፡ ቀድሞ ንግድ ፈቃድ የማውጣት አገልግሎት አሰጣጡ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ በመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ ለምሬት ይዳረግ ነበር፡፡ አሁን አገልግሎቱ ዘምኖ ኦንላይን በመሆኑ የህብረተሰቡን እንግልት አስቀርቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ አገልግሎቶች በኦንላይን የሚሰጡ መሆኑንም ወይዘሮ ሀቢባ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ አልፎ የመሰረታዊ ምርት ስርጭት አገልግሎት በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በህብረት ስራ ኮሚሽን የሚሰጥ ሲሆን ስድስት ክፍለ ከተሞች በቢሮው ስር ሆነው የመሰረታዊ ምርት ስርጭቱ በቴክኖሎጂ ተደግፎ ቤት ለቤት የሚሰጥበት አሰራር በሙከራ ደረጃ መጀመሩን ኃላፊዋ ገልፀዋል፡፡ ይህም ህብረተሰቡ በሲስተም ከተመዘገበ በኋላ ማኬባ በሚባል ድርጅት አማካኝነት የመሰረታዊ ምርት ስርጭት አገልግሎቱን ቤት ለቤት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። በዚህም ኮልፌ ቀራኒዮ 131 ሺህ 996፣ አዲስ ከተማ 81 ሺህ 834፣ ልደታ 54 ሺህ 402፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ 106 ሺህ 168፣ አቃቂ ቃሊቲ 49 ሺህ 521 እንዲሁም ጉለሌ 31 ሺህ 337 የህብረተሰብ ክፍሎች የመሰረታዊ ምርት ስርጭት አገልግሎቱን እያገኙ መሆኑን ኃላፊዋ አስረድተዋል፡፡

በንግድ ዘርፉ ያሉ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ መሰጠት በመቻላቸው በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለውጥ መምጣቱንም ኃላፊዋ ያነሳሉ፡፡ ቀድሞ የንግድ ፈቃድ የማውጣት አገልግሎት አሰጣጥ አሰራሩ ጎታች ነገሮች ነበሩበት። ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ በመሆኑም የንግዱ ማህበረሰብ ለምሬት ይዳረግ ነበር፡፡ አሁን አገልግሎቱ በመዘመኑ ወደ ንግድ ስርዓቱ ለመግባት ቀላል ነው፤ የህብረተሰቡን እንግልትም አስቀርቷል፡፡ ይህ ትልቅ ለውጥ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ወይዘሮ ሀቢባ እንደሚገልፁት፣ ቢሮው አገልግሎቶችን የሚሰጥበት ሲስተም ባለቤት የፌዴራል ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፡፡ ቀደም ሲል አልፎ አልፎ የሲስተም መቆራረጥ ያጋጥም ነበር፡፡ አሁን ላይ የሲስተም መቆራረጡ ተቀርፏል፡፡ በቀጣይም የሚሰጡትን አገልግሎቶች ይበልጥ በማጠናከር ህብረተሰቡ ያለምንም እንግልት ሁለንተናዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ፤ ህዝቡ ድረስ በመቅረብ ቤቱ ሆኖ አገልግሎትን የሚያገኝበት አሰራር ይበልጥ ማዘመን ላይ በትኩረት ይሰራል።

በ2017 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ ወር ባለው በከተማዋ ከ96 ሺህ በላይ አዲስ ንግድ ፈቃድ፣ ከ339 ሺህ በላይ የንግድ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 482 ሺህ 528 የንግዱ ማህበረሰብ ማህደር ስካን ተደርጎ በዲጂታል መንገድ ተደራጅቷል፡፡ በመዲናዋ 500 ሺህ ነጋዴዎች ሲኖሩ የፀና (በበጀት ዓመቱ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የተሰጠ አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ) ያላቸው 435 ሺህ 337 ነጋዴዎች መሆናቸውን ኃላፊዋ አስረድተዋል፡፡

## የአዲስ..

ከገጽ 15 የዞረ

“ሕጋዊ የፈጠራ ባለቤትነት ያገኘሁበትን በክር (በጥለት) በመጠቀም በእጅ የሚያመርቷቸው የተለያዩ አልባሳት (ቀሚስ፣ ሹራብ፣ ኮፍያ)፣ ጫማ፣ ቦርሳ፣ የሳሎን ምንጣፍ እና የመሳሰሉ ምርቶችን ለተጠቃሚዎች በብዛት እና በስፋት ለማዳረስ አቅጃለሁ፡፡ ሥራው የበለጠ መስፋት፣ ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል፣ የውጪ ገበያን ሠብሮ የመግባት አቅም ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ወደፊት የምርቶችን ዓይነት እና ጥራት በማሳደግና ብዛት እና ተደራሽነታቸውን በማስፋት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ነው፡፡ ከሥራ ማጣት የተነሳ እኔ ያሳለፍኳቸውን አስቸጋሪ ጊዜያት ሌሎች ሴቶች እና እናቶች እንዳያሳልፉ የድርሻዬን ለመወጣት ጥረት አደርጋለሁ” ያሉት የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 ነዋሪዋ ወይዘሮ ጤናዬ ተሰማ ናቸው፡፡

እየሠሩበት ያለውን የሕትመት ሥራ ዘርፍ ወደ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት (ጋርመንት) የመቀየር ጅምር እንቅስቃሴያቸውን ተፈፃሚ በማድረግ፤ የተሻለ የገበያ አማራጭ ባለው የሥራ ዘርፍ የመሠማራት ዕቅድ እንዳላቸው የጠቆሙት ደግሞ የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ነዋሪዋ ወይዘሮ ሞላሽ ናቸው። በአዲስ ለመሰማራት የመረጡት እና የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት (ጋርመንት) ራስን ከመጥቀም ባለፈ፤ ለብዙ ዜጎችም የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል መሆኑን በምክንያትነት አንስተዋል፡፡ “አስር የስፌት ማሽን ቢኖር፤ ለአስር ሠው የሥራ ዕድል መፍጠር ያስችላል” በማለት ዘርፉ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያለውን የተሻለ አቅም በምሳሌ አስረድተዋል፡፡

በመዲናዋ እየተተገበረ ያለው የምግብ ዋስትና ወይም የሴፍትኔት መርሃ ግብር የተጀመረው በ2009 ዓ.ም. መሆኑን ያስታወሱት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ የምግብ ዋስትናና ስራ ስምሪት ዘርፍ የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት የህብረተሰብ ተሳትፎ ቡድን መሪ አቶ አብርሃም መልኬ ናቸው፡፡

እንደ አቶ አብርሃም ገለፃ፤ በሁለት ምዕራፎች ተግባራዊ በተደረገው መርሃ ግብር በሺዎች የሚቆጠሩ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በእነዚህ ሁለት የመርሃ ግብሩ ምዕራፎች በአጠቃላይ ቁጥራቸው 674 ሺህ 397 የሚሆኑ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

አቶ አብርሃም አክለው እንዳብራሩት፤ በመርሃ ግብሩ የሚታቀፉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በአምስት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች በአካባቢ ልማት፣ ደረቅ ቆሻሻና ውበት፣ አነስተኛ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና፣ ከተማ ግብርና እንዲሁም በተፋሰስ ልማት ላይ ይሳተፋሉ፡፡ መርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎችን አስመርቆ መተው ብቻ ሳይሆን ከተረጅነት ወጥተው ራሳቸውን ችለው ለሌሎች ወገኖች የስራ እድል የሚፈጥሩበት ምቹ ሁኔታ መፍጠርንም ያካተተ ነው፡፡ ተጠቃሚ ዜጎች በመርሃ ግብሩ የተቀመጠውን ሥራ ከመከወን ባለፈ ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን ይሰራሉ፤ ቁጠባም ይቆጥባሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን በትናንትናው ዕለት ባደረገበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩን የ2017 በጀት ዓመት ሪፖርት አፈፃፀም ያቀረቡት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ በዘንድሮው ዓመት ሦስት ዓመት ለሞላቸው የሁለተኛ ምዕራፍ ተጠቃሚዎች የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግና ስልጠና በመስጠት 31 ሺህ የቤተሰብ ተወካዮችን በማስመረቅ የራሳቸውን ገቢ ወደሚፈጥሩበት ቋሚ የስራ መስክ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። ስለዚህ ለከተማዋ ዕድገት እንዲሁም ለዜጎች ተጠቃሚነት ከፍተኛ ሚና ያለውን ይህንን መርሃ ግብር የበለጠ ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡ በተለይ በመርሃ ግብሩ ከታቀፉ ዜጎች ትልቅ ኃላፊነት ይጠበቃል።

## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 1212/2018

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት በአስተዳደር ስር ለሚገኙ ለባለበጀት መስሪያ ቤቶች የተዘረዘሩትን ግዢዎችና አገልግሎት ስራዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል

- የፅህፈት መሳሪያ እና ሌሎች አላቂ የቢሮ እቃዎች
- ለቢሮ የሚሆን የመስተግዶ አቅርቦት
- አላቂ የፅዳት እቃዎች
- የተለያዩ መድረክ ማስዋብ /የዲኮር ስራ /
- ለሰራተኛ የሚሆን የደንብ ልብስና የተለያዩ የስራ ጫማዎች
- የቢሮ እድሳት ስራዎች እና ጥገና፣ ለቢሮ የሚሆን ፈርኒቸር፣ የቋሚና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የህትመትና የማስታወቂያ ስራ
- የህዝብ የትራንስፖርት መኪና
- የጭነት የመኪና ኪራይ
- የቢሮ/ህንጻ/ ማጠቃለያ ስራ
- የዶሮ ቤት ስራ /ኬጂ/
- የስፖርትና የጅምናዚየም ዕቃዎች
- የመኪና ሰርቪስና ጥገና
- በወረዳው ለሚከናወኑ ስራዎች የጉልበት ስራ

### ማሳሰቢያ:-

1. ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ስራ ፍቃድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና የቫት ሰርተፊኬት የዘመኑ ግብር የተከፈለበት ህጋዊ ማስረጃ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

2. ተጫራቾች ከላይ ከተዘረዘሩት ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች የሚወዳደሩ ከሆነ ለእያንዳንዱ ዘርፍ ያወጡት ህጋዊ የንግድ ስራ ፍቃድ በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡትን ሰርተፊኬት ማስያዝ ይኖርባቸዋል ፡፡

3. ተጫራቾች በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአቅራቢነት ሊስት ውስጥ የተመዘገቡ መሆን ይኖርባቸዋል ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ፡፡

4. ተጫራቾች የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች ከሆኑበት ጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁበትን እና ህጋዊ ሰርተፊኬት ከአደራጁ መስሪያ ቤት የተሰጣቸውን ወቅታዊ የድጋፍ ደብዳቤ ከሌሎች ዶክመንቶች ጋር አያይዘው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት በመደበኛ የስራ ሰዓት ከጽ/ቤቱ 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ

6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በጥንቃቄ በመስሪያ ቤቱ ፍላጎት መሰረት ብቻ በመሙላት የተሟላ የመወዳደሪያ ሰነድ ኦርጅናልና ኮፒ በሁለት የተለያየ ፖስታ በታሸገ ኢንቨሎፕ በማድረግ ማስገባት ይኖርባቸዋል የሚያስገቡት ዋጋ በነጠላ ቫትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

7. የጨረታ ሳጥኑ በአስረኛው ቀን ከቀኑ 11.30 ተዘግቶ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከጠዋቱ በ4.30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት በወረዳው ፋይናንስ ጽ/ቤት ይከፈታል፡፡

8. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፡፡ የአላቂ የቢሮ እቃ 25,000.00 የደንብ ልብስ 30,000.00 የኤሌክትሮኒክስ 35,000 የፈርኒቸር 25,000.00 የህትመት 15,000.00 የዲኮርና የሳውንድ 15,000.00 የተለያዩ ጥገናዎች 15,000.00 የትራንስፖርት 10,000.00 የመኪና ሰርቪስ እና ጥገና 15,000.00 የዶሮ ቤት ስራ /ኬጂ/ 15,000.00 የህንጻ ማጠናቀቅ ስራ 30,000.00 ብር / በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።

9. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹትን ማንኛውም ሁኔታ መለወጥ ወይም ማሻሻል ወይንም ከጨረታ ራሱን ማግለል አይችልም፡፡

10. ተጫራቾች አሸናፊ የሆኑባቸውን እቃዎች እስከ መስሪያ ቤቱ የንብረት ክፍል ድረስ በራሳቸው መጓጓዣና የጉልበት ወጪ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

11. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0115574183 በመደወል ወይንም ኦሎምፒያ አካባቢ ከጌቱ ኮሜርሻል ሴንተር በጀርባ በኩል ከሚገኘው ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ህንጻ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 1 በመምጣት መጠየቅ ይቻላል።**

---

በመንግስቱ ዶጀ ሚደቅሳ ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080117206 የሴሪ ቁጥር 070968 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ኮፒ (ካርታ) እና ማህደሩ ከመዝገብ ቤት ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኛል/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ማህደር አደራጅተን ተለዋጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ13/14986/08 ሴሪ ቁጥር 105832 በወ/ሮ ዝናሽ አበበ አለማየሁ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚኒየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ 19 ቀበሌ 55 በአዲሱ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር ---- በካርታ ቁጥር 12/31/16093/55938/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ለምለም ተስፋዬ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገኛል የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገኛል የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ ሁሉምታዬ በለጠ ጎሽሜ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090708670 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ 26/10/2017 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገኛል ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ወስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**







አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ምገባ ኤጀንሲ
Addis Ababa City Administration
Feeding Agency

## ራዕይ (Vision)

በ2022 ጥራት ደረጃውን የጠበቀ በምግብና ግብዓት በማቅረብ የከተማው ነዋሪዎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭነት ተቀርፎ አምራች ዜጋ ሆኖ ማየት፤

## ተልዕኮ (Mission)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለቤትነት በሚተዳደሩ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች እና የዕለት ጉርስ የሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ ምገባ፣ የተማሪዎች የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ በወጥነትና በፍትሐዊነት መቅረቡን በመከታተልና በመቆጣጠር የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ ፤ የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮችንና ተጋላጭነትን በመቀነስ እና በአዕምሮ የበለጸገ አምራች የሆኑ ዜጎች እንዲፈጠሩ ማስቻል ነው።።

## አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ እየሰራቸው የሚገኙ ዋና ዋና ስራዎች

- በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተማ 840,585 ተማሪዎችን በቀን ሁለት ጊዜ /ቁርስ እና ምሳ/ ይመገባል ።
- በሁሉም ክፍለ ከተማ በሚገኙ በ26 ተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ከ36,600 በላይ የዕለት ጉርስ የሌላቸው ዜጎች በቀን አንድ ጊዜ የምገባ አገልግሎት ያገኛሉ።
- ልጆቻቸውን በመንግስት ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ ከ16 ሺህ 400 በላይ መጋቢ እናቶች የስራ እድል ፈጥሯል።።
- ከ1,037,500 ከቅድመ አንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ደንብ ልብስ፣ 9,125,435 የመማሪያ ደብተር እና 9,125,435 የተማሪዎች ደብተር አቅርቧል።።

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ማህበራዊ ድረ ገፆች :-

- Facebook:https://www.facebook.com/61575251932855/posts/122094478412841731/?mibextid=rS40aB7S9Ucbxw6v
- Telegram:https://t.me/feedingagency8
- Tiktok:http://tiktok.com/@feeding.agency
- Twitter: https://x.com/feeding_agency?s=09
- Youtube፡https: https://youtube.com/@addisababacityadminstrationfa?si=QyoZiayxIloRxa5j
- Instagram፡https:https://www.instagram.com/reel/DIXXS2EoUTA/?igsh=NTc4MTlwNjQ2YQ==

# ተስፋን ያለመለሙ የስፖርት ማዘውተሪያዎች

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ ከገፀ ድር

በከተማዋ ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት ከተደረጉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መካከል በጥቂቱ

አዲስ አበባ ለመኖር ምቹ ከሆኑ ከተሞች ተርታ ለማሰለፍ የሚደረገው ጥረት እንደቀጠለ ነው፡፡ ለዚህም መዲናዋ ለእንቅልፍና ለእረፍት ጊዜ ያላት አትመስልም፡፡ መዲናዋ ብዙ እንቅልፍ አልባ ቀናትንና እረፍት አልባ ጊዜያትን እያሳለች ያለችው እንዲሁ በከንቱ አይደለም፡፡ ለኗሪዎቿ የተሻለና ምቹ የኑሮ ሁኔታ ለመፍጠር ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብዙ ርቀት ተጉዛለች፡፡

መዲናዋ፣ 'በቂ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የላትም' ለሚለው የዘመናት ቅሬታ ምላሽ ለመስጠት ያደረገችው ጥረት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ምቹ ባልሆኑ ሜዳዎችና ከባዶ እግር ባልተናነሱ ጫማዎች እግር ኳስን ጨምሮ ልዩ ልዩ ስፖርቶች የሚዘወተርባት ከተማ አዲስ አበባ፤ በስፖርታዊ ስፍራዎች ልማት ውስንነት ሳቢያ ይነሱ የነበሩ እነዚህ ክፍተቶች አሁን ምላሽ አግኝተዋል፡፡

የስፖርት መሰረተ ልማትን ማልማት ተፅዕኖው እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመገንዘብ ይረዳ ዘንድ አንድ መረጃ እንመልከት፡፡ አፍሪካን ስፖርት ኤንድ ክርኤቲቭ ኢኒሲቲትዩት (ASCI) የተሰኘው ዓለም አቀፍ የቢዝነስ ተቋም ከሁለት ዓመት በፊት የስፖርቱ ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ ዋጋን አስመልክቶ ያወጣውን መረጃ እዚህ ጋር እንጥቀስ። ተቋሙ ባወጣው መረጃ መሰረት በስፖርቱ ዘርፍ በዓመት እስከ 512 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይንቀሳቀሳል፡፡ ይህ አሐዝ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ውስጥ 624 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል ትንበያውን አስቀምጧል።

ስለ አህጉረ አፍሪካ ያወጣው መረጃ ደግሞ አግራሞትን ያጭራልና አንስተነው እንለፍ፡፡ አህጉሪቱ አሁን ላይ ከስፖርቱ እያገኘች ያለው ኢኮኖሚያዊ ድርሻ ከአንድ በመቶ በታች መሆኑ ሳያንስ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ደግሞ ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቀው ከስምንት በመቶ የተሻገረ አይደለም፡፡

ከጠቅላላ የህዝብ ብዛቷ ሰባ በመቶ የሚደርስ ወጣት ያላት አፍሪካ ከስፖርት ዘርፍ የምታገኘው ድርሻ በዚህ ደረጃ ላነሰበት ተቋሙ የተለያዩ ምክንያቶችን ቢጠቅስም የስፖርት መሰረተ ልማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ያለመሰራቱ ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ ይጠቅሳል። ኢትዮጵያም ከዚህ አንጻር ስትፈተሽ አሐዙ ከዚህ ቢያንስ እንጂ የሚሻል እንደማይሆን ጥርጥር የለውም፡፡

መነሻ ሀሳባችን ወደሆነው የአዲስ አበባ ስፖርት መሰረት ልማት ጉዳይ መለስ ብለን ስንቀጥል ከተማዋ ልዩ ልዩ የስፖርት ዓይነት የሚዘወተርባት ቢሆንም በቂ የሆነ የስፖርት ማዛውተሪያ ስፍራ አልነበራትም፡፡ ያሉትም ቢሆን ደረጃቸውን የጠበቁ አልነበሩም የሚለውን ሀቅ እናገኛለን፡፡ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በሚፈለገው ሁኔታ ባለመኖሩ ደግሞ በአዲስ አበባ ያለውን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እያዳከመውና ተተኪ ስፖርተኞች እንዳይፈጠሩ ከማድርጉም በተጨማሪ 'ከስፖርቱ ሊገኝ የሚችለው ትሩፋት እንዳይገኝ አድርጓል' የሚለው ቅሬታም መነሳት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ይሁንና ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጥያቄ ለመመለስ እንቅልፍ አልባዋ መዲና እያከናወነች ያለው ስራ በርካታ ነው። ተተኪ ስፖርተኞችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እንደዚሁም የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ለመፍጠር ድርሻው የጎላ እንደሆነ ደግሞ የከተማ አስተዳደሩ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን ይገልጻሉ፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት ከተማዋ በ11 ክፍለ ከተሞች ከ5 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎባቸው የተገነቡ የልማት ፕሮጀክቶችን ለአገልግሎት ክፍት ያደረገች ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 122ቱ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ናቸው። ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥም 1 ሺህ 530 የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ስለመገንባታቸው ተገልጿል።

ፕሮጀክቶቹ ለአገልግሎት ክፍት በሆኑበት ዕለት ጉዳዩን አስመልክቶ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ "ህፃናት እና ወጣቶች እንኳን ደስ አላችሁ፤ ይገባችኋል" ብለዋል፡፡ አክለውም፣ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንዲሉ እነዚህ ደረጃውን ጠብቀው የተገነቡት ልማቶች 50 በመቶ ወጪያቸው የተሸፈነው በማህበረሰቡ መሆኑ ልዩ ያደርጋቸዋልም" ማለታቸው ይታወሳል፡፡

በእርግጥም ዝግጅት ክፍላችን እንደተመለከተው በርካታ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በዘመናዊ የሜዳ ንጣፍ ተሸሞንሙነው ለከተማዋ ነዋሪዎች ጀባ ተብለዋል፡፡ አብዛኞቹ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በምሽት ጨዋታ እንዲደረግ የሚያስችል መብራት ጭምር የተገጠመላቸው ናቸው፡፡ በበጋው ወቅት አቧራማ ክረምት ሲገባ ደግሞ የሚጨቀዩት ሜዳዎች ዛሬ ላይ መልካቸው ተቀይሯል፡፡

ስለ ስፖርታዊ ማዘውተሪ ስፍራዎች ያነጋገርናቸው ወጣቶች አስተያየትም ይህንኑ ያጠናክራል፡፡ ወጣት በረከት ሙሉነህ አስተያየታቸውን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ከአጋሩ ወጣቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው "አሁን ላይ የቅርጫት ኳስና እግር ኳስ የምንጫወትባቸው ሜዳዎች ምቹ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም ግን በአብዛኛው የምንጫወተው የመኪና መንገድ በመዝጋት በመሆኑ ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል፡፡ ለከፍተኛ ጉዳትም እንዳረግ ነበር፡፡ ከተሽከርካሪ ጋር እየተጋፈጥን ጭምር ነበር የምንጫወተው"፡፡

በአካባቢያቸው የነበረው ሜዳ ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ይጫወቱ እንደነበር የሚገልፀው ወጣት በረከት፣ አንዳንድ ጊዜም መጫወቻ ሜዳ ፍለጋ ከአካባቢያቸው ርቀው ለመሄድ ይገደዱ እንደነበርም ያስረዳል፡፡

'የአዲስ ተስፋችን እግር ኳስ ፕሮጀክት' መስራችና አሰልጣኝ መሐመድ ናስር በበኩሉ ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጋር በተያያዘ በሰጠን አስተያየት የመዲናዋ ወጣቶች ደረጃቸውን በጠበቁ መጫወቻ ሜዳዎች በሚኖሩበት፣ በሚማሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትልቅ ዕድል ፈጥሯል ይላል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአካባቢው በብዛትና በጥራት መኖር የአዳጊ ፕሮጀክቶች የወጣቱን ጤንነት በመጠበቅ፣ አካል ለመገንባት እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ስፖርተኞችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል ሲል ጨምሮ ተናግሯል፡፡

ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ተደርጎባቸው በመዲናዋ እየተሰሩ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የእግር ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስ፣ የመረብ ኳስን ጨምሮ 17 አይነት ስፖርታዊ አገልግሎቶችን ሊሰጡ ስለመሆናቸው ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከሰሞኑን ለአገልግሎት ክፍት የተደረጉትን 22 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በተጨማሪ ከዚህ ቀደም ተጠናቅቀው ወደ አገልግሎት ከገቡ መሰል ስፍራዎች መካከል በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የሚገኘው አልማዝዬ ሜዳ ሁለገብ የስፖርት ማዘወተሪያ፣ ቦሌ ገርጂ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኘው የእግር ኳስ ሜዳ እና የፈረንሳይ ለጋሲዮን ኳስ ሜዳ የወጣቶች እና ህጻናት የመጫወቻ እና የስፓርት ማዘውተሪያ ስፍራ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የማዕከላትና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አስተዳደር ልማት ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ባዩ በበኩላቸው በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየተገነቡ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እና የስፖርት ዓይነቶች ያካተቱ መሆናቸው ቀደም ሲል ከነበሩት የተለዩ ያደርጋቸዋል ብለዋል። ይህም ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት እንዲሁም ጤናው የተጠበቀ እና አምራች ዜጋ ለመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ይዞ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የነበሩት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ለተሰሩበት ዓለማ ብቻ እንዲውሉ የሕግ ከለላ እንዳልነበራቸውና እየፈረሱ ለሌላ ዓላማ ይውሉ እንደነበር ጠቁመዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ አሁን ላይ ደንብና መመሪያ ጭምር እንደተዘጋጀ አቶ ብርሃኑ ይገልጻሉ፡፡ የተዘጋጀው ደንብም ዓላማው ቦታዎቹ ለሌላ ዓላማ እንዳይውሉ ጥበቃና ከለላ ማድረግ፣ ከህገ ወጥ ወረራ በመከላከል ደህንነታቸውን መጠበቅ፣ አገልግሎት መስጠት ከጀመሩም በኋላ ባለሙያዎችን በመመደብ በአግባቡ ማስተዳደር ያስችላል ሲሉም የደንቡን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡ እንዲሁም ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ለህዝብ ጥቅም ተብሎ በልማት ሲነሳ ምትክ ቦታ እንዲዘጋጅላቸው ደንቡ ያስገድዳል፡፡

በትምህርት ቤቶች ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከትምህርት ሰዓት ውጪ ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር የተዘረጋ ሲሆን፣ ለዚህም ከትምህርት ቢሮ ጋር በተደረሰ ስምምነት ስፍራዎቹ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በኩል አስፈላጊው እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው አቶ ብርሃኑ ያስረዳሉ፡፡

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የከተማ አስተዳደሩ የመጫወቻና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር ወደ 5 ሺህ ለማድረስ ዕቅድ ይዞ በመስራት ላይ እንደሚገኝ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መረጃ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም የሜዳ ተንከባካቢ፣ ጥበቃ እና የጽዳት ሰራተኞችን በመመደብ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ጥራት ለመጠበቅ በቋሚነት እንደሚሰራ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡